ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ
84ኛ ዓመት ቁጥር 090 ኅዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “ለኢትዮጵያ እድገትና ብልፅግና በጋራ መቆም ክብር ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ከግልና ከአንድ አካባቢ መሻትና ፍላጎት ይልቅ ለኢትዮጵያ ብልፅግና እና እድገት በጋራ መቆም ክብር ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 19ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አርባ ምንጭ ከተማ ትናንት ሲከበር እንደገለጹት፤ እኛ ኢትዮጵያውያን በጋራ ስንቆም ውብና ጠንካራ እንሆናለን፡፡ ከግልና ከአንድ አካባቢ መሻትና ፍላጎት ይልቅ ለኢትዮጵያ ብልፅግና እና እድገት በጋራ መቆም ክብር ነው፡፡

አብሮነታችንን በምንም ሁኔታ የማንሸረሽር ሕዝቦች እንሁን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ በመደመር እሳቤ በኅብረ ብሔራዊ ትርክት በጋራ ለመቆም ሁሉም ዜጋ እንዲወስንም ጠይቀዋል፡፡

ኢትዮጵያን አውቀን አልጨረስናትም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ የጋራ ታሪክ፣ የጋራ ባሕል፣ የጋራ ውርስ እና የጋራ መስዋዕትነት መኖሩንም ገልጸዋል፡፡

ገዢ ትርክትን በማጎልበት ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸው፤ ኅብረ ብሔራዊነት ኢትዮጵያን ለመገንባት እና ለማጽናትም የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል መከበር ሚናው የጎላ መሆኑን አውስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ትልቅ መጽሐፍ ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ÷ በውስጧ በርካታ ባሕሎች፣ እሴቶች፣ እውቀቶችና ጥበቦች እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡

አንድ መጽሐፍ ብቻውን ሙሉ እንደማይሆን ሁሉ የኢትዮጵያ ብሔሮችም አብሮነትን በማጎልበት ጉድለቶችን መሙላት እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ተቀድታ የማታልቅ ባሕር በመሆኗ በቁንጽል እውቀት ከመበየን ይልቅ በቅርበት ሆኖ ማጥናት፣ መመራመርና ማወቅ ይገባል ብለዋል፡፡

ልባችን ወደ ሠላም በመመለስ ኢትዮጵያን ይበልጥ

“ለኢትዮጵያ እድገትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በዓሉ የአንድነትና የኅብረ-ብሔራዊነት ቀለም መገለጫ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል የአንድነት፣ የሠላም፣ የመቻቻል እንዲሁም የኅብረ-ብሔራዊነት ቀለም መገለጫ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በዓሉን አስመልክቶ ትናንት ባስተላለፈው መልዕክት፤ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በየዓመቱ መከበሩ፤ የሕዝቦች ትስስርን በማጠናከር ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትን በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲገነባ ከማገዙ ባሻገር የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባሕላቸውንና ማንነታቸውን ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥራል ብሏል፡፡

በዓሉ የአንድነትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ሀገር በቀል እውቀትና ሥርዓተ ትምህርቱ

**ዋለልኝ አየለ**

**ዜና ትንታኔ**

በርካታ ሀገራት ሀገር በቀል እውቀቶቻቸውን በማዳበርና በማዘመን የእድገትና ሥልጣኔያቸው መነሻ አድርገዋል። ሀገር በቀል እውቀቶችን በሥርዓተ ትምህርታቸው በማካተት ይበልጥ እንዲጎለብቱና ከዘመን ጋር እንዲራመዱም ያደርጋሉ፡፡

በኢንዶኔዥያ የጊያካርታ ዩኒቨርሲቲ ‹‹የሀገር በቀል ዕውቀት እና የሳይንስ ውሕደት ለባሕል ቀጣይነት›› በሚል ርዕስ እኤአ በ2018 በተሠራ ጥናት፤ ሳይንስ ከሀገር በቀል እውቀት የተቀዳ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ እንደ ጥናቱ ገለጻ፤ ሳይንስ ማለት በተፈጥሮ የሚከሰቱ ክስተቶችን መረዳት ማለት ነው፡፡ ይህም አካባቢን በማስተዋል እና በሕይወት ዘመን ልምድ በማዳበር በተፈጥሮ የሚከናወኑ ነገሮችን የማወቅ ውጤት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ እና የዓለም አቀፍ ቅርሶች ባለቤት ናት፡፡ በኪነ ሕንጻ፣ በመድኃኒት፣ በግብርና፣ በአልባሳት እና በሌሎች የዕደ ጥበብ ሥራዎች የራሷ ሀገር በቀል

ሀገር በቀል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አዲስ አበባ የቱሪዝም ትንሳዔ ላይ ናት

ገጽ 2



ዜና

# 388 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረገው የካርበን ሽያጭ

**ማርቆስ በላይ**

የደን መራቆት ችግር የአየር ሁኔታን በማዛባት ለተፈጥሮ አደጋዎች ከማጋለጥ ባሻገር ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳት እንዳለው ይገለጻል። በተለይም የሀገሪቱን የልማት እንቅስቃሴ ለማሳካትም የደን ዘርፉ እድገት ወሳኝ መሆኑ ይገለጻል። የተራቆተ መሬትን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግም መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን የጋራ ርብርብ ይጠይቃል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጎዱ አካባቢዎችን በደን ለመሸፈንና እንዲያገግሙ ለማድረግ የአረንጓዴ ዐሻራን መርሐ ግብርን ጨምሮ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው። የደን ሽፋንን ለማሳደግና አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችም እየተሠሩ ይገኛል። ታዲያ ለመሆኑ የተራቆተ መሬትን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ምን ይመስላሉ።

በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ፕሮጀክቶች አስተባባሪ አቶ ወርቅነህ ያደሳ እንደገለጹት፣ የተራቆተ መሬትን መልሶ እንዲያገግም በማድረግ የሁምቦና የሶዶ አርሶ አደሮች ብቻ ከካርቦን ሽያጭ አንድ ነጥብ 18 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘታቸውን ይናገራሉ።

የተራቆተ መሬትን መልሶ እንዲያገግም የሚያስችለው ፕሮጀክት በስምንት ክልሎች በሚገኙ 37 ወረዳዎች ላይ እየተተገበረ መሆኑን የገለጹት አስተባባሪው፣ እስካሁን ከ268 ሺህ ሄክታር በላይ መሬትን መልሶ ማልማት መቻሉንም ነው የገለጹት።

ፕሮጀክቱ አካባቢውን ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ መልሶ እንዲያገግሙ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፣ ይህም የአፈር መሸርሸርን መቀነስ፣ የሰብል ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ለእንስሳት መኖን ጨምሮ፣ ብዝኃ ሕይወትን ለመጨመርና የአርሶ አደሩንም ገቢ ለማሳደግ እንደሚያስችል ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ 388 ሺህ ሰዎች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ በፕሮጀክቱ ትግበራ ዙሪያ ሥልጠና ለአርሶ አደሮች መሰጠቱንም ያስረዳሉ።

ፕሮጀክቱ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በመካከለኛው ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በአፋር ክልሎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝም በመግለጽ፣ ፕሮጀክቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ ለሚገኘው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ትልቅ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን አስተባባሪው ገልጸዋል።

በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ 4 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር የተራቆተ መልክዓ ምድርን መልሶ እንዲያገግም ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በአካባቢው የሰዎች ባለቤትነት ስሜት ባለመኖሩ ምክንያት የደን ዛፎችን ለማገዶነትና ለመኖ በመጠቀም መሬቱ ባዶ ቀርቶ እንደነበር የሚገልጹት ደግሞ የሆቢቻ በዳ ወይጦ ተራራ ደን ልማትና ጥበቃ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር ሰብሳቢ አቶ መኮንን ጉጆ ናቸው።

በአካባቢው የታየውን የደን መራቆት ተከትሎ ድርቅ፣ የምርት መቀነስ፣ የውሃ እጥረትና የእንስሳት ሞት ተከስቶ እንደነበር በመግለጽ፣ የተራቆተው መሬት መልሶ ለማልማት በተደረገው ጥረት በአካባቢው የደን ሽፋን ማደግ መቻሉን ይናገራሉ።

በማኅበር በመደራጀት ደኑን የመጠበቅ ሥራ መሥራታቸውንና ከደን ልማቱ የካርበን ሽያጭ ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በየዓመቱ ከሚገኘው ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በመጠቀም የልማት ሥራዎችን እንደሚሠሩ፣ ወፍጮ ቤት ማቋቋማቸውንና ለትምህርት ቤቶች እገዛ ማድረጋቸውን ያስረዳሉ።




# ኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም አሰባሳቢና አቃፊ ሥርዓት ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- ኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአብሮነት ለመኖር የመሠረቱት አሰባሳቢና አቃፊ ሥርዓት መሆኑን የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ።

19ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል "ሀገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ በአርባምንጭ ከተማ ትናንት በድምቀት ተከብሯል።

አፈ ጉባዔ አገኘሁ ተሻገር በዓሉ ላይ እንደገለጹት፤ የፌደሬሽን ምክር ቤት ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ለማስከበር ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል።

ምክር ቤቱ በዋናነት እንደ ሀገር የብዝኃነት አያያዝ እንዲጎለብት፣ አብሮነትና ወንድማማችነት ሥር እንዲሰድ ሲሠራ መቆየቱንና አሁንም እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለፉት 18 ዓመታት በዓሉ በተከታታይ መከበሩ በሀገራዊ አንድነት ግንባታ ላይ ውጤት እያስገኘ መሆኑን ገልጸው፣ ይህም ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት አስተዋፅዖ የጎላ መሆኑን ገልጸው፤ በተጨማሪም በሕገ-መንግሥት ላይ የነበረ የግንዛቤ ክፍተትን ለመሙላት በዓሉ የአስተምሕሮ መድረክ ሆኖ እያገለገለ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በዓሉ ሁሉም የሀገሪቷ ሕዝቦች ማንነታቸው እንዲከበር እንዲሁም ለፍትሕና ለነፃነት መረጋገጥ በጋራ እንዲሠሩ አድርጓል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ ይህ ደግሞ ኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአብሮነት ለመኖር የመሠረቱት አሰባሳቢ፣ አቃፊና አሳታፊ ሥርዓት መሆኑንም ያረጋገጠ ነው ብለዋል።

በዓሉ መከበሩ በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲጠናከርና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጎለብት ያደረገ መሆኑን አመልክተው፤ በተለይም ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ የተከበሩ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓላት የሕዝቡን አብሮነት ለማጽናት ማስቻላቸውን አፈ ጉባዔ አገኘሁ አስረድተዋል።

በመንግሥት ደረጃም ከልዩነት ይልቅ አብሮነት ለማጽናት፣ ከመራራቅ ይልቅ ለመቀራረብ የሚያስችሉ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን አስታውሰዋል። በዓሉ ለፍትሕ፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲሁም ለሕገ መንግሥት አስተምሕሮ መሠረት የጣለ መሆኑንም ነው የገለጹት።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ በበኩላቸው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል የፍቅር ምንጭና የአንድነት መሠረት መሆን ችሏል። የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል በአርባ ምንጭ ከተማ የሩቅና የቅርብ ጠላቶችን ተስፋ በሚያስቆርጥ መልኩ በድምቀት ተከብሯል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ውበትና ፀጋ የሚታደሉት እንጂ የሚታገሉት አይደለም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ብልፅግና ፈተናዎችን አልፎ ተስፋ ያላትና አስተማማኝ ሀገር እንድትሆን አስችሏል ነው ያሉት።

ሀገራዊ ለውጡ ከይስሙላ ፌዴራሊዝም ወደ እውነተኛ ፌዴራሊዝም ያሸጋገረ እንዲሁም ነጠላ ትርክትን ወደ ብሔራዊ ትርክት በመቀየር ቱሩፋት እንዳስገኘ ገልጸው፤ ለዚህ ክልሉ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት መጠናከርና ማጎልበት የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣም ነው የተናገሩት።

በዓሉ "ሀገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት በደማቅ ሁኔታ መከበሩን ኢዜአ ዘግቧል።

# አዲስ አበባ የቱሪዝም ትንሳዔ ላይ ናት

**ዳንኤል ዘነበ**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሐ-ግብሩ ለቱሪዝም ዘርፉ በተሰጠው ከፍተኛ ትኩረትና በኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም ትንሳዔ ላይ እንዳለች የአዲስ አበባ ከተማ የባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለይ የኮሪደር ልማቱ ትሩፋቶች የሆኑት የዓድዋ ሙዚየም፤ ልዩ ልዩ የመስሕብ ቦታዎች፣ ማራኪ እይታዎች እና የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች አዲስ አበባ ከተማን ለዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ስብሰባዎች እንድትመረጥ አድርጓታል፡፡ በዚህም አዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም ትንሳዔዋ ሆኗል ብለዋል፡፡

እንደ ሂሩት (ዶ/ር) ገለጻ፣ የኮሪደር ልማቱ ከቱሪዝም ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ነው። የኮሪደር ልማቱ ቅርሶችን አጉልቶ በማውጣት፣ የበለጠ በመጠበቅ፣ በማደስና በመጠገን ፊት ለፊት መጥተው እንዲታዩ አድርጓል፡፡ ይህም አንድ የቱሪስት ከተማ ማሟላት ያለባትን መስፈርት እንድታሟላ አስችሏታል።

የኮሪደር ልማቱ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን የቱሪስቶችን ደኅንነት መጠበቅ የሚያስችሉ የደኅንነት ካሜራዎችን፣ የመንገድ መብራቶችና አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ያሟላ መሆኑም ከተማዋ ለቱሪስት ምቹ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ከ2011 ዓ.ም ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማን የቱሪዝም ልማት ሥራዎች ለማስፋፋት በርካታ ተግባራት መከናወናቸው ጠቅሰው፤ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ የባሕል፤ ኪነጥበባት እና የቱሪዝም ማዕከላት ከተማዋ



በሀገር ውስጥ ሆነ በውጭ ጎብኚዎች ተፈላጊ እንድትሆን አድርገዋታል ብለዋል ።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሐፍታይ ገብረ እግዚአብሔር እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከለውጡ ወዲህ የከተማዋን የቱሪዝም ልማት ሥራዎች ለማስፋት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ከእነዚህም መካከል አንድነት ፓርክ፣ እንጦጦ ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም እና በከተማዋ የተለያዩ አከባቢዎች እየተካሄደ የሚገኘው የኮሪደር ልማት ተጠቃሽ ናቸው ።

የልማት ሥራዎች የቱሪዝም ሀብቶች እንዲገለጡና ይበልጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስቻላቸውን ጠቅሰው፤ በአዲስ አበባ የተሠሩት የልማት ሥራዎችም ለከተማዋ አዲስ ገጽታን በማላበስ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከፍተኛ መነቃቃት መፍጠራቸውን አቶ ሐፍታይ ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማዋ አሁን ላይ በርካታ የዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ስብሰባዎችን ለማከናወን ቀዳሚ ተመራጭ እየሆነች መምጣቷንም ገልጸዋል። በቅርብ ጊዜያት የተከናወኑ የአፍሪካ የመከላከያ ሚኒስትሮች ስብሰባ፣ ዓለም አቀፍ የፈጠራ ውድድሮች፣ የካፍ ጉባዔን ጨምሮ የከተሞች ፎርምን ለአብነት ጠቅሰዋል።

አዲስ አበባን ወደ ኮንፈረንስ ቱሪዝም ከተማነት የማሸጋገር ዕቅድ ተይዞ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ነው ያሉት አቶ ሐፍታይ፣ በዚህም የተከናወኑና በመከናወን ላይ የሚገኙ የልማት ተግባራት መዲናዋ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ምቹ ከተማ እንድትሆን አስችለዋታል ብለዋል፡፡

# ክልሎችን ከክልሎች የሚያገናኙ የአውሮፕላን መዳረሻዎች እየተስፋፉ ነው

**ዋስልኝ አየለ**

አዲስ አበባ፡- ክልሎችን ከክልሎች በቀጥታ የሚያገናኙ የአነስተኛ አውሮፕላን መዳረሻዎች እየተስፋፉ መሆኑን የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን አስታወቀ። በአሁን ጊዜ አነስተኛ አውሮፕላኖች የሚያርፉባቸው 23 መዳረሻዎች ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ አመልክቷል።

በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ እንዳለ አሰፋ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በሀገር ውስጥ በረራዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ አዲስ አበባ ከዋናው አውሮፕላን ማረፊያ መምጣት የግድ ነበር። አሁን ጊዜ አነስተኛ አውሮፕላኖች የሚያርፉባቸው 23 መዳረሻዎች ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። መዳረሻዎቹን ቁጥር ከዚህ በላይ ለማሳደግና ሁሉንም የሀገር ውስጥ አካባቢዎችን ለማገናኘት ተጨማሪ መዳረሻዎች እየተገነቡ ነው፤ የዲዛይን ጥናት እየተደረገባቸው የሚገኙ እንዳሉም ሥራ አስፈፃሚው ተናግረዋል።



እንደ አቶ እንዳለ ገለጻ፤ መዳረሻዎቹ በጥናት የተሠሩ እና ለአነስተኛ አውሮፕላኖች ማረፊያ የሚያገለግሉ ቢሆኑም፤ በቀጣይ ግን ተርሚናል ተሠርቶላቸው ወደ ኤርፖርትነት የሚያድጉ ናቸው። ይህም መዳረሻዎቹን በተለይም ለኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው ያስችላል።

በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በመንገድ ችግር ምክንያት አርሶ አደሩ ምርቱን በርካሽ ዋጋ በመሸጥ የልፋቱ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ገልጸው፤ የአነስተኛ አውሮፕላኖች መዳረሻ መስፋፋት ለእነዚህ አርሶ አደሮችና ለሀገሪቱም ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አስረድተዋል።

‹‹ኤርፖርቶች እንዳሉ ሆኖ፤ ትኩረት እያደረግን ያለነው ኤርስትሪፕ (መዳረሻ) ላይ ነው›› ያሉት አቶ እንዳለ፤ ዋና ዓላማው ገጠራማ ሆነው የአውሮፕላን ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሆነ አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ጥናት አድርጎ ፈቃድ ከሰጠ በኋላ በክልሎች ወይም በግል ዘርፎች ወይም በኤርፖርቶች ድርጅት ሊገነባ ይችላል። መዳረሻዎቹ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል ለመሄድ ወደ አዲስ አበባ ይደረግ የነበረውን በረራ ከማስቀረታቸውም ባሻገር፤ ከአንድ የቱሪዝም መዳረሻ ወደ ሌላ የቱሪዝም መዳረሻ በቀጥታ በመሄድ የቱሪዝም ዘርፉን ያጠናክራሉ ብለዋል።

እንደ ኬንያ ባሉ ጐረቤት ሀገራት እስከ 200 የሚደርሱ መዳረሻዎች እንዳሉ የገለጹት አቶ እንዳለ፤ የሀገር ውስጥ የአነስተኛ አውሮፕላኖች መዳረሻ (ኤርስትሪፕ) ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሁሉንም አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የአውሮፕላን መዳረሻዎቹ መስፋፋት ለአርሶ አደሩ የግብርና ምርቶችን በቀላሉ ለገበያ ለማቅረብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ተብሏል።



# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ከመኸር እርሻ ከ16 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰበሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 መኸር እርሻ እስካሁን ድረስ 16 ሚሊዮን 449 ሺህ 133 ኩንታል ምርት መሰብሰቡን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የክልሉ ግብርና ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዓለምይርጋ ወልደሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 መኸር እርሻ 550 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን 49 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ እስካሁን ድረስም 252 ሺህ 732 ሄክታር መሬት ላይ ያለ ሰብል ተሰብስቧል፡፡ ከዚህም 16 ሚሊዮን 449 ሺህ 133 ኩንታል ምርት ተገኝቷል፡፡

በክልሉ ቆላማ አካባቢዎች ለስብስባ የደረሰ 360 ሺህ ሄክታር መሬት ሰብል ተለይቶ ርብርብ እየተደረገ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ እስካሁን ድረስ 252 ሺህ 732 ሄክታር መሬት ላይ ያለ ሰብል ተሰብስቧል፡፡

በዚህም ውስጥ 3 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ከአዝርዕት ሰብሎች፣ 12 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ደግሞ ከሆርቲካልቸር ልማት በድምሩ 16 ሚሊዮን 449 ሺህ 133 ኩንታል ምርት ተገኝቷል ብለዋል፡፡

አርሶ አደሩ በተለይ የአዝርዕት ሰብሎችን ሰብስቦ ሳይወቃ የማቆየት ልምድ ስላለው ቁጥሩ ከላይ ከተጠቀሰው ሄክታር መሬት የተገኘውን ሙሉ ምርት የሚያሳይ እንዳልሆነም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ክልል የተያዘውን እቅድ ለማሳካት በሜካናይዝድ የታገዘ የማሳ ዝግጅት፣ የግብዓት አቅርቦት እና የሰብል ተባይ ጥበቃ ሥራዎችን ያጠቃለለ ዝግጅት ሥራ መከናወኑን አስታውሰው፤ ከዚህም በተጨማሪ የኩታ ገጠም እርሻ ላይ ትኩረት ተደርጎ ተሠርቷል ነው ያሉት፡፡

በተጠቀሰው ወቅት በዘር ከተሸፈነው 550 ሺህ ሄክታር መሬት ውስጥ 170 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆነው በኩታ ገጠም የተዘራ ነው፡፡ አሁን ላይ በአብዛኛው የክልሉ ሞቃታማ አካባቢዎች በመኸር የተሠሩ ሰብሎች ምርት እየደረሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ቀሪ ምርቶችም ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲሰበሰቡ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ለምርት አሰባሰቡም የማኅበረሰቡን ጉልበትና ምቹ በሆነባቸው አካባቢዎች ላይ ደግሞ ከ95 በላይ ኮምባይነሮች ገብተው እንዲሰበስቡ እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪም ብዙ ባልተለመደው የፀደይ እርሻ በመኸር ተዘርተው ቀድመው የደረሱ በቆሎና ጤፍ ሰብሎችን በማንሳት 35 ሺህ ሄክታር መሬት በሽምብራ ዘር መሸፈን መቻሉን ጠቁመው፤ ይህም የአርሶ አደሩን በዓመት ሁለት ሦስት ጊዜ የማምረት ልምድ እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ ሽምብራ ብዙም ግብዓት የማይፈልግ፣ በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ ምርት መስጠት የሚችል እንዲሁም በራሱ የናይትሮጂን የማብላላት አቅም ስላለው ለመሬት ለምነት መጨመርም ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ነው ብለዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ የምርት አሰባሰቡ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አርሶ አደሩ አሁንም በእያንዳንዱ ቀን ማሳ ሆኖ የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡ እንዲሰበስብ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡


# በኮሪደር ልማቱ ከ600 በላይ አውቶብሶችና ታክሲዎችን የሚያስተናግዱ ተርሚናሎች ተገንብተዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት በአንድ ጊዜ ከ600 በላይ አውቶብሶችና ታክሲዎችን ማስተናገድ የሚችሉ ተርሚናሎች መገንባታቸውን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ አስታወቀ። ከ185 በላይ የታክሲና የአውቶብስ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎች መሠራታቸውንም ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ያብባል አዲስ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ አስተዳደሩ አዲስ አበባን ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከተማ ለማድረግና ለማዘመን የኮሪደር ልማት እያካሄደ ነው። በመጀመሪው ዙር የኮሪደር ልማትም ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የትራንስፖርት ዘርፉን ማዘመን ሲሆን በዚህም ከ600 በላይ አውቶብሶችና ታክሲዎችን የሚያስተናግዱ ተርሚናሎች ተገንብተዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በልማቱ ለሞተር አልባ ትራንስፖርት በተሰጠው ትኩረት በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት 100 ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የእግረኛ እና ከ100 ኪሎ ሜትር በላይ የብስክሌት መንገድ ተገንብቷል። ይህም የሞተር አልባ ትራንስፖርት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል ።





አቶ ያብባል አዲስ

እንደ ከተማ እስካሁን የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አለመጀመሩን የጠቆሙት አቶ ያብባል፤ ቢሮው የብስክሌት ኦፕሬተሮችን መፍጠር የሚያስችል የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ አዘጋጅቷል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ አደረጃጀቱና የአሠራር መመሪያው ተግባራዊ ሲሆን በከተማ አስተዳደሩ የብስክሌት መጋራት የትራንስፖርት ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል ብለዋል።

ከሃያት ወደ ሲኤምሲ፤ ከሜክሲኮ ወደ ሣር ቤት፤ ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ ከፍተኛ መኪና ተጠቃሚ ማኅበረሰብ እንደነበር አውስተው፤ በኮሪደር ልማቱ የእግረኛ መንገድ ከተገነባ ወዲህ አጫጭር መንገድ ተጓዦች ታክሲ ከመጠበቅ ይልቅ በእግራቸው መጓዛቸው የዘርፉን አገልግሎት ያሳደገ ስለመሆኑ አቶ ያብባል ገልጸዋል።

በኮሪደር ልማቱ መንገዶች የተሳፋሪዎች የመጫኛና የማውረጃ ቦታ እንዲኖራቸው መደረጉን የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ ይህ ትናንት ያልነበረ ዛሬ ላይ የሚታይ እና ዘርፉን ወደ ዘመናዊነትና ተወዳዳሪነት የሚያመጣው መሆኑን አመልክተዋል።

ከተፈቀደ የመጫኛና ማውረጃ ቦታ ውጭ መጫንና ማውረድ አይቻልም። ይህ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻልም የትራንስፖርት እንቅስቃሴው ሠላማዊና የተቀላጠፈ እንደሚሆን አብራርተዋል።

ከ185 በላይ የታክሲና የአውቶብስ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎች በመጀመሪያው የኮሪደር ምዕራፍ መገንባታቸውን ያስታወሱት አቶ ያብባል፤ በከተማዋ ከአሁን በፊት የመኪና ማቆሚያ (ፓርኪንግ)፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ተርሚናሎችና በርከት ያሉ ፓርኪንግ እንዳልነበረ ተናግረዋል። አሁን ላይ በለውጡ መንግሥት የመስቀል አደባባይ፤ አንድነት ፓርክ፤ ዓድዋ ድል መታሰቢያ የመሳሰሉ የመኪና ማቆሚያዎች (ፓርኪንግ) መገንባታቸው አስታውቀዋል።

በመጀመሪያው የኮሪደር ልማት ብቻ 32 መኪና ማቆሚያዎች (ፓርኪንጎች) መገንባታቸው ያስታወቁት ቢሮ ኃላፊው፤ በሁለተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ቤዝመንትና ከዚያ በላይ መሠረት ባላቸው ሕንጻዎች ጭምር እየተሠሩ ያሉ መኪና ማቆሚያዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ከ58 በላይ ፓርኪንጎች የሚሠሩ ሲሆን ለከተማዋ ዘመናዊነትና ተወዳዳሪነት ብሎም ለተቀላጠፈ የትራንስፖርት አገልግሎት እና የትራፊክ ፍሰት መሻሻል ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ነው ያሉት።

በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት በአንድ ጊዜ ከ600 በላይ አውቶብሶችና ታክሲዎች ማስተናገድ የሚችሉ ተርሚናሎች መሠራታቸውን የተናገሩት አቶ ያብባል፤ በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ፕሮግራም ሰፋፊ የተርሚናል ግንባታ እቅዶች ታቅደው እየተሠሩ መሆኑን አመልክተዋል።

# ፖሊሲው ለገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ወሳኝ ሚና ይኖረዋል

**ማሕሌት አብዱል**



አዲስ አበባ፡- አዲሱ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ በአግባቡ መተግበር የገጠር መዋቅራዊ ሽግግርን በፍጥነት እውን ለማድረግ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ሀገሪቱ ተግባራዊ እያደረገች ለምትገኘው የኢኮኖሚ ማሻሻያ (ሪፎርም) ውጤታማነት መሠረት የሚጥል እንደሆነም ተመልክቷል።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ዳይሬክተር ታደለ ማሞ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ በአዲሱ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ በተሟላ መንገድ መተግበሩ በገጠር ሁለንተናዊ እና መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማምጣት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ በቅርቡ ይፋ ያደረገችው የኢኮኖሚ ማሻሻያ (ሪፎርም) ውጤታማነት ፖሊሲው መሠረት የሚጥል ነው።

በዋናነትም ፖሊሲው ከሀገሪቱ ሕዝብ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆነው አርሶ አደር የግብርና ሥርዓት በማዘመን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ብሎም ለኢንዱስትሪው ሁነኛ መጋቢ ሆኖ እንዲቀጥል፤ ሰፊው የሰው ኃይል በማኑፋክቸሪንግና በአገልግሎት ዘርፉ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የማድረግ ዓላማ ሰንቆ የተቀረፀ መሆኑን ታደለ (ዶ/ር) አመልክተዋል። ለዚህም ደግሞ በዝናብና በበሬ ላይ የተንጠለጠለውን የአመራረት ሂደት ወደ መስኖና መካናይዜሽን እርሻ በመቀየር፤ በምርምርና በቴክኖሎጂ በመደገፍ በጥቂት አርሶ አደሮች ብቻ በማምረት የገጠሩ ክፍል መዋቅራዊ ሽግግር በወሳኝነት ማሳለጥ እንደሚያስችልም ጠቁመዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ ግብርና መዋቅራዊ ሽግግር በሚመጣበት ወቅት አምስት በመቶ ብቻ የሚሆነው አርሶ አደር ቀሪውን 95 በመቶ የሚሆነውንና በከተማ የሚኖረውን ሕዝብ እንደሚመግቡ፤ የማምረት ሂደቱም በቴክኖሎጂ እየተመራ ኢንዱስትሪውን ይደግፋል። ኢንዱስትሪውም ለግብርናው ዘርፍ ግብዓት እንደሚያቀርብ ታሳቢ ተደርጎ ነው የተነደፈው። የኢንዱስትሪው ዘርፍ ሲያድግ ግብርናን ያንቀሳቅሰዋል፤ የፊትዮሽና የኋልዮሽ ግንኙነታቸውንም ያስፋፋል። ከዚህ አኳያም የግብርና ገጠር ትራንስፎርሜሽን እንዲመጣ ሌሎቹም በተመጣጣኝ መልኩ ማደግ አለባቸው።

«ግብርና ብቻውን የቱንም ያህል ቢያድግ ኢንዱስትሪውና አገልግሎት ዘርፉ ካላደገ ትርጉም የለውም» ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ሲያድግም እንደማዳበሪያ፣ መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የሚስፋፉበት ዕድል ስለሚፈጠር አርሶ አደሩ በቀላሉ ግብዓት ተጠቅመው ምርታቸውን ለማሳደግ እንደሚያስችላቸው አስገንዝበዋል።

የምርምር ተቋማት ምርት የሚያሳድጉ አዳዲስ ምርምሮችን በማፍለቅ፤ ግብርና ኤክስቴንሽኑ አርሶ አደሩን በመደገፍ፤ የአገልግሎት ዘርፉ መጠናከር እንዲሁም እንደ መብራት፤ መንገድና ውሃ ያሉ መሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በተሟላ መልኩ ማከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን አብራርተዋል።

«ፖሊሲው ያስቀመጠው አቅጣጫ ብቻ ነው፤ በተጨባጭ በገጠር መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ ግን ግልፅ የሆኑ የማስፈፀሚያ ስልቶችና መመሪያዎች በተዋረድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል» የሚሉት ታደለ (ዶ/ር)፤ ለዚህም በፖሊሲው ዋነኛ ዓላማ ዙሪያ ከከፍተኛ እስከ ታችኛው ያለ መንግሥታዊ መዋቅር ላይ እንዲሁም ለዘርፉ ተዋናዮች ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በተጨማሪም ፖሊሲውን በተጨባጭ መሬት ላይ ለማውረድም ሆነ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሀገርን ሠላም የማስጠበቁ ሥራ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባም አሳስበዋል።

# “ለኢትዮጵያ እድገትና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለማበልፀግ በጋራ እና በትብብር እንሥራ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ በፈጣሪ ቸርነት እና በዜጎቿ ትጋት የጀመረችውን የብልፅግና ግስጋሴ ከግብ እንደምታደርስም አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሴራ፣ የፀብ፣ የውጊያ እና የጥላቻ ትጥቅን ፈትቶ ለኢትዮጵያ ሠላም እና ዕድገት በጋራ መሥራት እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል ታጣቂዎች ከጦርነት ሠላም ይሻላል ብለው ወደ ሠላም መምጣታቸውን አስታውሰው፥ ይህን መልካም ጅማሮ በኦሮሚያ፣ አማራ እና በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ታጣቂ ወንድሞች እንዲከተሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

19ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አርባ ምንጭ ከተማ ትናንት በስኬት የተከበረ ሲሆን መጪው ዓመት የ20ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን አዘጋጅ ክልል የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መሆኑ ታውቋል።

# በዓሉ የአንድነትና የኅብረ-ብሔራዊነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በ1987 የፀደቀው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የብሔር ብሔረሰቦችን መብት የሚያረጋግጥ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና የባሕላዊ መግለጫዎችን አስፈላጊነትን አፅንዖት መሆኑንም ጠቅሷል።

በዓሉ የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች በታሪክ ለሀገሪቱ የበለፀገ የባሕል ቅርስ አስተዋፅዖ ያበረከቱትን አንድነት አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት ተግባብተውና ተስማምተው የኖሩ የሕዝቦቿን የዳበሩ ባሕሎች፣ ቋንቋዎችና ትውፊቶችን ይበልጥ እንዲደምቁ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁሞ፤ ይህ ሀገራዊ መግባባትን በእጅጉ እንደሚያጠናክረው ነው የገለጸው፡፡

የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ይህን ልዩነት ለማክበር እና የማይናወጥ ብሔራዊ ማንነትን እንዲጎለብት ከማድረጉም ባሻገር በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል አብሮነትን ለማጠናከር ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ነው ያለው፡፡

ሀገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት የሚለው መሪ ሃሳብ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ እውነታዎችን ቁልጭ አድርጎ እንደሚገልጽም አንስቷል፡፡

የዘንድሮ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል በአርባ ምንጭ ከተማ እንዲከበር ማዘጋጀቱ ክልላዊ ብዝኃነትን እና አካታችነትን ለማስተዋወቅ ያለውን ቁርጠኝነት እንደሚያሳይም አብራርቷል፡፡

“በዓሉ የአንድነት፣ የሠላም፣ የመቻቻል እንዲሁም የኅብረ-ብሔራዊነት ቀለም መገለጫ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያውያን የብዝኃ ባሕል፣ ታሪክ፣ እሴትና የተፈጥሮ መስኅብ መሆናቸውን ለዓለም የሚያስተዋውቁበት መድረክ እንደሆነ መገንዘብ እንደሚያስፈልግም የሚኒስቴሩ መረጃ ያመላክታል፡፡

# ሀገር በቀል እውቀትና ሥርዓተ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እውቀት አላት። ዳሩ ግን እነዚህ ሀገር በቀል እውቀቶች በዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካተው ሥራ ፈጣሪ እና ማንነትን አስቀጣይ አለመሆናቸው ይነገራል።

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕል ጥናት መምህር እና የባሕል ተመራማሪ የሆኑት ሰሎሞን ተሾመ (ዶ/ር) በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ሀገር በቀል እውቀቶች ማኅበረሰቡ ለዘመናት ያካበታቸው የራሱ ዕውቀቶች ናቸው። የማኅበረሰቡ ሕይወት ናቸው፤ ማንነቱን የሚያስቀጥልባቸውም ናቸው።

«ሥርዓተ ትምህርቱ መጀመሪያውኑም የማኅበረሰቡን ባሕል፣ ሥነ ልቦና እና ዕውቀት የረሳ ነው» የሚሉት ሰሎሞን (ዶ/ር)፤ ከውጭ የተቀዳ በመሆኑ የኢትዮጵያን እምቅ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል እንዳልሆነ ያብራራሉ። የራስን ማንነትና የፈጠራ ጥበብ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት የምርጫ ጉዳይ እንዳልሆነም ይናገራሉ።

እንደ ሰሎሞን (ዶ/ር) ገለጻ፤ ሀገር በቀል እውቀትን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት ሲባል፤ የውጭውን አለመጠቀም ማለት አይደለም። ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን የሀገራትን ተሞክሮ መውሰድ ያስፈልጋል፤ ሆኖም ግን የራስን ጥሎ ከሆነ «ቤት መሥራትን ከመሠረቱ ከመጀመር ይልቅ ከጣሪያ እንደመጀመር ይሆናል» ይላሉ። ወደ ዓለም መሄድ የሚቻለው መጀመሪያ የራስን አውቆ ነው። በተለይም ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ባለው፤ ተማሪዎች ሀገራቸውን እንዲያውቁ መሠራት አለበት ይላሉ።

«የዕደ ጥበብ ሥራዎችን በትምህርት ቤቶች ማሳየትና ማለማመድ ያስፈልጋል» የሚሉት ሰሎሞን (ዶ/ር)፤ ተማሪዎች ለትልልቅ ሥራ ፈጠራዎች የሚነሳሱት በአካባቢ የሚሠሩ ነገሮችን በማየት እንደሆነ ይናገራሉ። እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ተማሪዎች የማይሰበር ጀበና መሥራት የሚችሉት፤ መጀመሪያ የሚሰበረውን የሸክላ ጀበና አሠራር ሲያውቁትና ሲያዩት ነው። ሞፈርና ቀንበርን በዘመናዊ መሣሪያ መቀየር ያልተቻለው፤ ተማሪዎቹ መጀመሪያ የእንጨቱን ሞፈርና ቀንበር አሠራር እንዲያዩትና እንዲያውቁት ስላልተደረገ ነው። መማሪያ ክፍል ውስጥ የሞፈርና ቀንበር አሠራር፣ የሸክላ አሠራር ቢማሩ፤ እነዚህን የሚተካ ሌላ ነገር ወደ ማሰብ ይሄዳሉ። ዘመናዊ የልብስ አሠራር ሊፈጥሩ የሚችሉት፤ መጀመሪያ የሽመና ጥበብ ቢማሩ ነበር። የቤት ውስጥ የመገልገያ ዕቃዎችን ከኬሚስትሪና ከፊዚክስ ጋር አያይዞ እንዲማሩ አለመደረጉ ሥራ ፈጣሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል ይላሉ።

ሰሎሞን (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ መስጊድ እና ቤተ ክርስቲያን የታነፁባቸው ሀገር በቀል የኪነ ሕንጻ ዕውቀቶች ነበሩ፤ ዳሩ ግን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካተው ወደ ትውልድ ስላልተላለፉ የአሁኑ ትውልድ ሊሠራቸው አልቻለም።

የዩኒቨርሲቲዎችንና የኢንዱስትሪዎችን ትስስር በተመለከተም ሰሎሞን (ዶ/ር) ሲናገሩ፤ ትስስሩ መሆን ያለበት ከውጭ ሀገር የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ጋር ሳይሆን ሽሮ ሜዳ ከሚገኝ የራስ ሀገር ጥበብ ጋር ነው። ይህን ለማድረግ እንዲያስችል ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱ ወጣቶችን የክህሎቱ ባለቤት ማድረግ እንደሚገባው ያሳስባሉ።

ባለፈው ዓመት በአሜሪካ ዋሽንግተን ታኮማ ዩኒቨርሲቲ «ሀገር በቀል እውቀትን በትምህርት ውስጥ ማካተት» በሚል ርዕስ በታተመ ጥናት እንደተገለጸው፤ እውቀት ማለት የሰዎች፣ የተፈጥሮና የባሕል ነፀብራቅ ቢሆንም፤ ይህ ግን በቅኝ ግዛት አጋጣሚዎች ይሸረሸራል። ቅኝ ገዥ ሀገራት በቅኝ ተገዥዎች ላይ በሚያደርሱት የባሕል ለውጥ ሀገር በቀል እውቀቶች በሌላ ሀገር ባሕል ይቀየራሉ። ይህም ለነባሩ ነዋሪ አዲስ እንዲሆንበት ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በቅኝ ያልተገዛች ሀገር ብትሆንም፤ ሥርዓተ ትምህርቱ የውጭውን መሠረት ያደረገ እና ለሀገር በቀል እውቀቶች ትኩረት ያልሰጠ መሆኑ በራስ ፈቃድ ቅኝ መገዛት መሆኑን ምሑራን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ቅኝ ያልተገዛችው የራሷ ነባር ባሕልና ማንነት ያላት በመሆኑ እና ቅኝ ገዥዎች በቀላሉ እንደማይበርዙት አጥንተው መሆኑን የታሪክ ተመራማሪው አቶ አበባው አያሌው ተናግረዋል።

የአሜሪካው ጥናት እንደሚለው፤ ሀገራት ሥርዓተ ትምህርት የሚቀርጹት፤ ሀገር በቀል እውቀቶችን መነሻ በማድረግ ነው። ይህ ግን በዘመናት ሂደት እየተሻሻለና እየተወራረሰ ይሄዳል። በተለይ ቅኝ ተገዥ ሀገራት ሥርዓተ ትምህርታቸውን ወደ ሀገር በቀል እውቀቶች ለመመለስ ይቸገራሉ።

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ «ሀገር በቀል ዕውቀት በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ» በሚል ርዕስ ተሾመ አበራ በሚባሉ አጥኚ በተሠራ ጥናት፤ በኢትዮጵያ በተለያዩ ሥርዓተ መንግሥታት ውስጥ የነበረው የትምህርት ሥርዓት፤ እውነተኛውን የኢትዮጵያን ባሕል፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያንፀባርቅ አይደለም። ለዚህም ምክንያቱ ከምዕራባውያን የሚገለበጥ መሆኑ ነው። ከ1900 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ ሥርዓተ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከውጭ የተገለበጠ ሲሆን፤ የውጭ ባለሙያዎችም ያሉበት ነው።

ጥናቱ በማጠቃለያው እንደሚጠቁመው፤ ሀገር በቀል ዕውቀቶች ዕውቅና ሊሰጣቸውና ወደ ሥርዓተ ትምህርቱ ሊካተቱ ይገባል። ለሀገር በቀል ዕውቀቶች የሀገር ውስጥ ቋንቋ ወሳኝ ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ አሁንም በእንግሊዝኛ መሆኑ የሀገር በቀል እውቀትን እንደሚጎዳ እና የተማሪዎችን አመለካከት ጭምር ወደ ውጭ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የማኅበረሰብ ጉድኝትና ሀገር በቀል እውቀት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ሠላም ዓለሙ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ትምህርት ሚኒስቴር ሀገር በቀል እውቀቶች ማንነትን ለማስቀጠል፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ለሥራ ፈጠራ ያላቸውን ፋይዳ አምኖበት ጥናት እየተደረገ ነው።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ በየዘርፉ ያሉ ሀገር በቀል እውቀቶችን ማኅበረሰቦች እየተጠቀመባቸው መሆኑን፣ በየትኛው አካባቢ ምን አይነት ሀገር በቀል እውቀቶች እንዳሉ እና እንዴት እንደሚጠቀሙበት እየተጠና እና ልየታ እየተደረገበት ነው። የባሕል መድኃኒት ከሆነ፤ ለምን መድኃኒትነት እንደሚጠቀሙበት፣ በምን አይነት አካባቢና መልክዓ ምድር ውስጥ እንደሚገኝ፣ ምን አይነት ሰዎች ናቸው የሚያውቁት የሚለውን በተመራማሪዎች ይታያል ብለዋል። በቃል ደረጃ እየተላለፉ የመጡትን ወደ ሰነድ የማምጣት እና በሳይንሳዊ ሙያ የመለየት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በመድኃኒት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በአልባሳት፣ በማኅበረሰብ ፍልስፍና በመሳሰሉት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በየአካባቢያቸው እንዲያጠኑ አቅጣጫ መሰጠቱን እና እስከ አሁንም 17 ያህል ዘርፎች እንደተለዩ የተናገሩት ወይዘሮ ሠላም፤ ጥናቱ በሂደት ላይ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን፣ ሀገር በቀል የፖለቲካ አካሄድን ተግባራዊ እያደረገች እንደመሆኗ ለውጥ እያመጣች እንደሆነ ሁሉ ሀገር በቀል እውቀቶችን በትምህርት ሥርዓቷ በማካተት በኢኮኖሚው በፈጠራውና በመሰል ዘርፎች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የዘርፉ ምሑራን ይጠቁማሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከእያንዳንዱ የታሪክ ክስተት በስተጀርባ ያሉ እውነታዎች ዛሬን በአግባቡ እንድንጠቀም ዕድል የሚሰጡን ናቸው!

የዛሬውንም ሆነ ያደሩ ችግሮቻችንን ለዘለቄታው ፈትተን በአዲስ መንገድ መጓዝ ካልጀመርን ብዙ ትውልዶች ሲያልሙት የኖሩትን ሀገራዊ ብልፅግና ልንፈጥር አንችልም። ይህን ማድረግ ካልቻልን እንደ ሀገር ያለን ሕልውና አደጋ ውስጥ ስለመሆኑ ለዚህ ትውልድ መነገር ያለበት አጀንዳ አይደለም።

እኛ ኢትዮጵያውያን የብዙ ጥሩ እና መጥፎ ታሪኮች ባለቤቶች ነን። በጥሩዎቹ አንገታችንን አቅንተን በልበ ሙሉነት እንደምንጓዘው ሁሉ፤ በመጥፎዎቹ አንገታችንን ደፍተን በተሰበረ ልብ መንቀሳቀሳችን የማይቀር ነው። ይህ እንኳን ረጅም የሀገረ መንግሥት ታሪክ ላላት ሀገር እና ሕዝብ ቀርቶ በግለሰብ ሕይወት ውስጥ ሊያጋጥም የሚችል ነባራዊ ክስተት ነው።

የነገሮች ጥሩና መጥፎነት በአብዛኛው ከማኅበረሰብ የአስተሳሰብ ዕድገት ጋር የሚቆራኝ፤ የምዘና ስሌቱን ይህንን ታሳቢ ያደረገ እንደሚሆን ይታመናል። ታሪክ እና የታሪክ ክስተቶችን ለዛሬው ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ዕድገት መማሪያ ሆነው ሲያገለግሉ መሠረት የሚያደርጉት ይህንን ተጨባጭ እውነታ ነው።

ትናንት ውስጥ ያሉ በጥሩም ሆነ በመጥፎ የሚነሱ ማኅበራዊ ክስተቶች፤ በአንድም ይሁን በሌላ ዘመኑን የገዙ አስተሳሰቦች ውጤቶች ናቸው። እነዚህን ክስተቶች ዛሬ ላይ ቆመን ዛሬን በሚዋጀው የአስተሳሰብ ስሌት በመጥፎ እየፈረጅን ለዛሬዎቻችን የጥፋት ምንጭ ልናደርጋቸው አይገባም።

ይህ ታሪክ እና የታሪክን ጠቀሜታ በትክክል ካለመገንዘብ የሚመነጭ፤ አጠቃላይ የሆነውን የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ዕድገት እና ዕድገቱ አሁን ላይ ይዞት የመጣውን የህሳብ ልዕልና በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው። ዛሬ የብዙ መጥፎ እና ጥሩ የትናንት ክስተቶች ድምር ውጤት መሆኑን ያለመገንዘብ ጭምር ነው።

የእያንዳንዱ ዘመን የአስተሳሰብ ልኬት የሚወሰነው ዘመኑ በደረሰበት የአስተሳሰብ ልኅቀት፤ አስተሳሰቡ በፈጠረው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እሳቤ ነው። የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓትን ምን ይመስል እንደነበር፤ ሥርዓቱን እና ሥርዓቱ የፈጠረውን ማኅበራዊ መስተጋብር ልንማር እንችላለን።

ስለፊውዳሊዝም ሥርዓት ሆነ ሥርዓቱ ስለፈጠረው ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ተምረን ስለ ሥርዓቱ ያለንን ግንዛቤ ልናሳድግ እንችላለን፤ ለዛሬ የሚጠቅመንን ካገኘን ልንወስድ እንችላለን፤ ከዚህ ወጥተን ያለፈውን ሥርዓቱን በማውገዝ ሆነ የሥርዓቱን ባሕሪያት በመኮነን የምናተርፈው ነገር አይኖርም።

ስለ ትናንት የሚኖረን አስተምሕሮም ሆነ ትርክት ዛሬያችንን ለማበላሸት ሳይሆን፤ ከትናንት ተምረን ዛሬን የተሻለ ለማድረግ ነው። የትናንት ስህተቶቻችን አርመን ከስህተት አዙሪት ለመውጣት ነው። ይህ ደግሞ እንደ ማኅበረሰብ የተሰጠን ተፈጥሯዊ ፀጋ ነው። ዛሬን የተሻለ ለማድረግ ያለን ትልቁ አቅማችን ነው።

ዛሬ ላይ እንደ ሀገር ያለን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብርም የዚህ ተጨባጭ እውነታ ነፀብራቅ ነው። የዛሬ ፖለቲካዊ እሳቤያችንን ብንወስድ እንኳ፣ በበጎም ይሁን በመጥፎ የሚነሱ እንደ ሀገር የመጣንባቸው የረጅም ዘመናት የተለያዩ የፖለቲካ እሳቤዎቻችን ድምር ውጤት ነው።

ዛሬ ላይ ስለመደመር የፖለቲካ እሳቤ የምናወራው፣ በየዘመኑ የነበሩ ሀገራዊ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ምን ይመስሉ ነበር፣ ለምን ስኬታማ አልሆኑም..ወዘተ የሚሉትን ጠይቀን በተቻለው ሁሉ ለጥያቄዎቹ ተጨባጭ መልስ ለመስጠት ሞክረን ነው ። ከዚህም አልፎ ከመጥፎው ተምረን በጎውን ደግሞ ደምረን ለመጓዝ ነው፡፡ እንደ ሀገር የመጣንባቸውን የፖለቲካ ሥርዓቶች እና የአስተሳሰብ መሠረታቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ገምግመንም ነው።

የቀደሙት ሆኑ የአሁኑ ትውልድ ስለሀገሩ ያለውን በጎ መሻት/የበለፀገች ሀገር የማየት ተስፋ እውን ለማድረግ፤ የትናንት መጥፎም ሆነ ጥሩ ታሪካችን ራሳችንን በተሻለ መልኩ እንድናውቅ የሚረዱን የመማሪያ መጽሐፍቶቻችን ናቸው። ከእያንዳንዱ የታሪክ ክስተት በስተጀርባ ያሉ እውነታዎችም ዛሬን በአግባቡ እንድንጠቀም ዕድል የሚሰጡን ሊሆኑ ይገባል።

እነዚህ እውነታዎች እንደሀገር ለጀመርነው የብልፅግና ጉዞ ስኬት ትልቅ አቅም ተደርገው የሚወሰዱም ናቸው። ይህንን እውነታ በልኩ ተረድቶ መንቀሳቀስ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው። ይህንን ማድረግ ከቻለን ከግጭት አዙሪት ወጥተን ፤ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶችን መሻት እውን በማድረግ የበለፀገች ሀገር መፍጠር እንችላለን!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያ-በሌማት ትሩፋቱ በረከት

መልካምሥራ አፈወርቅ

ኢትዮጵያ ምድረ-ለምለም ይሏት ድንቅ ሀገር ነች:: የተራራዎቿ ጉያዎች የተሸሸገ ፀጋ አላቸው:: ከዓመት ዓመት የሚፈሱ ወንዞቿ በበረከት ተሞልተዋል:: ንፁሕ አፈሯ የዘሩበትን ያበቅላል:: በወጉ እጅ ያልነካቸው ማዕድናት ተዝቆ የማያልቅ ሀብትን ሸሽገው ይዘዋል:: ኢትዮጵያ- ተፈጥሮን ከአዕምሮ ጥበብ አጣምራ፣ በተጓዘች ጊዜ ለዓለም ተዓምር ሊያስብሉ የሚቻላቸውን ድንቅ እሴቶች ማሳየት ብርቋ አይሆንም::

ይህች አገር ለዘመናት ከኋላዋ ሲከተላት የኖረው የድርቅና ረሀብ ታሪኳ በቀላሉ ሳይፈዝ ዓመታት ተቆጥረዋል:: እንዲያም ሆኖ ድንቅ ተፈጥሮዋ ዘወትር አብሯት ነው:: ዛሬም ይሁን ቀድሞ «ሁሉ በእጇ፣ ሁሉ በደጇ» ስለመሆኑ ድፍን ዓለም አሳምሮ ያውቃል:: እንደ ጥንቱ «የዳቦ ቅርጫት» ናት ባትባልም ፀጋ በረከቶቿን አላጣችም::

እነሆ! ይህች ድንቅ ሀገር ካቀረቀረችበት ቀና የሚያደርጋትን የትንሳዔ ጉዞ ጀምራለች:: በመዳፏ ያሉ በረከቶች ውሃ ያነሱ ይዘዋል፣ በምድሯ የፈሰሱ ሀብቶች ከልካቸው ሊገኙ ጊዜው ደርሷል:: ኢትዮጵያ ዛሬም ጥቁር አፈሯ ምግብ፣ ነፋሻ አየሯ መድኅን ሆኖ ሕዝቦቿን ጤና አውሎ ያሳድራል::

ሀገራችን ለግብርናው ልማትና ለእንስሳ ሀብት አመቺ የሚባልን ምኅዳር ተችራለች:: ያላትን ዕምቅ ሀብት በወጉ መጠቀም ላይ ግን ብዙ እንደሚቀራት ጥናቶች ያረጋግጣሉ:: መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በብሔራዊ ደረጃ የተመዘገበው ዓመታዊ የወተት ምርት 7 ነጥብ 1 ቢሊዮን ሊትር ነው:: ዓመታዊው የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ደግሞ ከ66 ሊትር የበለጠ እንዳልሆነ ይታወቃል:: ይህ ማለት ለአንድ ሰው በዓመት ከሚያስፈልገው የወተት ድርሻ እጅግ አነስተኛውን መጠን የያዘ መሆኑን ያመላክታል::

ይህ እውነታ ኢትዮጵያ እንደ አማራጭ የተቀነባበሩ የወተት ተዋፅዖዎችን ከውጭ ሀገራት እንድታስገባ ያስገድዳታል:: በዚህ ምክንያትም በየዓመቱ ከ25 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር በላይ ታወጣለች:: በዕንቁላልና የዶሮ ሥጋ ምርትም ሀገራችን መልካም የሚባል ሀብትና ምቹ ሁኔታዎች አሏት ቢባልም ተጠቃሚ መሆን ግን አላስቻላትም:: ሀገራችን በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ናት:: በቂ ወተትና ተዋፅዖዎቹን የማግኘት ዕድሉን ግን ተነፍጋለች::

በኢትዮጵያ ከሚገኙ ዕንቁላል ጣይ ዶሮዎች መካከል 75 በመቶው ያህሉ በዓመት በአማካይ የሚጠበቅባቸውን ያህል አያስገኙም:: በሌሎች ሀገራት ግን የምርቱ ሂደት በዘመናዊ አሠራር በመታገዙ ከአንድ ዶሮ በዓመት 270 ዕንቁላሎችን ማግኘት ይቻላል:: ተጠቃሚዎቹም የዶሮ ሥጋን እንደልብ በመመገብ የሚያህላቸው የለም:: እነዚህና መሰል እውነታዎች ኢትዮጵያ ተዘናግታ ከቆየችባቸው ኋላ ቀር ልማዶች እንድትነቃ ደወል ሆኗል::

ሀገራችን ድንቅ የተፈጥሮ ሀብትና ምርት በእጇ እያለ በወጉ ያለመጠቀሟ ሐቅ ለዘመናት ዋጋ አስከፍሏታል:: እስከ አሁን እንደ ዕምቅ ሀብቶቿ ብዛት ያሻትን ያህል እጇን አልሰደደችም:: በእልፍ በረከቷና በደጇ ሞልቶ ሊፈስ በሚችል ፀጋዋም የበይ ተመልካች ሆና ቆይታለች:: አሁን ግን ይህ ታሪክ በ«ነበር» ሊሻር ጊዜው ደርሷል::

> **ሀገራችን ድንቅ የተፈጥሮ ሀብትና ምርት በእጇ እያለ በወጉ ያለመጠቀሟ ሐቅ ለዘመናት ዋጋ አስከፍሏታል:: እስከ አሁን እንደ ዕምቅ ሀብቶቿ ብዛት ያሻትን ያህል እጇን አልሰደደችም:: በእልፍ በረከቷና በደጇ ሞልቶ ሊፈስ በሚችል ፀጋዋም የበይ ተመልካች ሆና ቆይታለች:: አሁን ግን ይህ ታሪክ በ‹‹ነበር›› ሊሻር ጊዜው ደርሷል**

እነሆ! ዛሬ ሀገራችን የመሶቧ ሙላት ለሌሎች ጭምር እንዲተርፍ የለውጥ ጉዞ ጀምራለች:: በሌማት ትሩፋት መርሐግብር ያሏት ፀጋዎች በወጉ ተለይተዋል:: በዚህ ዘርፍ በሚመዘገቡ ውጤቶችም ኢኮኖሚውን ማሻሻል ከሚቻልበት አግባብ እየተደረሰ ነው:: በመርሐግብሩ ከእንስሳት፣ ከዓሣና ከማር ሀብት የሚገኘውን ፀጋ በወጉ በመጠቀም ኅብረተሰቡን መድረስ የሚቻልበት አሠራር ዕውን መሆን ጀምሯል::

አርብቶ አደሩን ከከተሜው ሳይለይ በአንድ ከሚያዛምደው የሌማት ትሩፋት ቋርሶ የማይጎርስ የለም:: ሁሉም በፀጋው በረከት እጁን ሰዶ ሊሳተፍ በገበታው ዙሪያ ተገኝቷል:: ብዙዎች በግልና በማኅበር ተደራጅተዋል:: ቀድሞ በዓይን ብቻ የሚያውቁት በ«ነበር» የሚሰሙት ትሩፋት ዛሬ ከሌማታቸው ተርፎ፣ ለሌሎች ጭምር ሊደርስ የገቢ ምንጫቸው ሆኗል::

አሁን በዘመናዊ የንብ ቀፎ በኪሎግራም ማር የሚቆርጡ፣ ከዶሮዎች በረከት በሺዎች ዕንቁላል የሚቆጥሩ፣ በወተት ምርታቸው አይብ ከቅቤ የሚዝቁ፣ በርክተዋል:: የሌማት ትሩፋቱ አንዱ መገለጫ ጥራትን ከፍጥነት እውን ማድረግ ነው:: ምርታማነትን በማዘመንም ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነትን ይተገብራል:: በኦሮሚያና ሲዳማ ክልሎች አካባቢዎችን በመንደር ከማደራጀት ባለፈ፣ ቴክኖሎጂን የመተግበር ሥራዎች ተከውነዋል:: በዚህም የተሻለ ገቢን ማሳደግና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ተችሏል:: በመርሐ ግብሩ የተለየ ትኩረት መኖሩ በኅብረተሰቡ አኗኗር ላይ መልካም የሚባል ለውጥን አምጥቷል:: ለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ ከሃያ ስድስት ሺህ በላይ የማምረቻ መንደሮች አስተዋፅዖ አበርክተዋል::

በሲዳማ ክልል በአንድ ዓመት ብቻ የዕንቁላል ምርት ቁጥሩ ከ3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ወደ 3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ማደግ ችሏል:: በተመሳሳይም የሥጋ ምርት ከ94 ሺህ ቶን ወደ 122 ሺህ ቶን ከፍ ብሏል:: የኑሮ ውድነትን ለመቋቋምና ሕይወትን በተሻለ ለመምራት ዋነኛ መንገድ የሆነው የሌማቱ ትሩፋት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መታገዙ በርካታ ችግሮችን ለመቅረፍ ቀኝ እጅ እየሆነ ነው::

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚጠቁመው በ2017 በጀት ዓመት በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር ሦስት ቢሊዮን 503 ሊትር ወተት ተገኝቷል:: 37 ነጥብ ስድስት ሺህ ቶን የዓሣ ምርትም ተመዝግቧል:: በተመሳሳይ በማር ምርት የተገኘው ውጤት 42 ነጥብ 19 ሺህ ቶን መድረሱን ያመላክታል::

በያዝነው ዓመት በወተት ምርት 12 ቢሊዮን 116 ሊትር ለማምረት ታቅዶ በአራት ወራት ውስጥ 3 ቢሊዮን 503 ሊትር ለማግኘት ተችሏል:: በዚህ ዘርፍ በኩል የሚኖረውን ምርታማነት ለማሳደግ የወተት ላም ዝርያን ማሻሻልና በመኖ አቅርቦቱ ላይ ትኩረት ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል:: የወተት የዶሮ፣ የእንቁላልና የዓሣ ምርቶችን ለማሳደግም በሀገር አቀፍ ደረጃ መርሐ ግብር ተቀርፆ መተግበር ጀምሯል:: በያዝነው ዓመት አራት ወራት በነበረው ክንውንም 37 ነጥብ ስድስት ሺህ ቶን የዓሣ ምርትና 42 ነጥብ 19 ሺህ ቶን የማር ምርት ማግኘት ተችሏል:: 2 ቢሊዮን 853 እንቁላልና 56 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋም የትሩፋቱ በረከት ሆኖ ተመዝግቧል::

የሌማት ትሩፋት ዋና ዓላማ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ነው:: ለተጠቃሚው የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል:: ይህ ትሩፋት አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ከሸማቹ የማገናኘት ትስስርም አለው:: እንዲህ ዓይነቱ እውነታ ሀብት በማሳባሰብ ረገድ ለሚኖረው ሂደት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚሉት በቀጣዮቹ ዓመታት የሚተገበረው የሌማት ትሩፋት በወተት፣ በዶሮና በማር ምርቶች ላይ ትኩረቱን ያደርጋል:: በዚህም የሥርዓተ ምግብ ችግሮች እንዲቀረፉና የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ዕድሉን ያሰፋል:: ወደውጭ የሚላኩ ምርቶችን በማበራከትም በውጭ ምንዛሪ የሚገቡትን አቅርቦቶች ለማስቀረት ያስቻላል ::

በሀገራችን መተግበር የጀመረው የሌማት ትሩፋት «ኢትዮጵያ» ከሚለው ስም ቀጥሎ ስንጠራበት የኖርነውን ክፉ ስያሜ ከስሩ ነቅሎ የማስቀረት ኃይል አለው:: ሀገራችን የችግርና ረሀብ ምሳሌ ለምትመስላቸው ሁሉ ትሩፋቱ በአካል የሚታይ፤ በተግባር የሚፈተሽ ታላቅ በረከት ሆኖ ተረጋግጧልና::

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# አንድነታችንን አጠንክረን ፤ኅብረ-ብሔራዊነታችንን ማግዘፍ ይጠበቅብናል

ክብረ መንግስት

ሀገር በሰው፤ ሰውም በሀገር ይመሰላል:: አንዱ በአንዱ ውስጥ ይገለጣል:: ይህንን በጋራ የመጽናታቸውን ምስጢር ከምናይባቸው ኩነቶች መካከል ሕዳር 29 የምናከብረው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል አንዱ ነው:: ዕለቱ ሲሰየም የተለያዩ ትርጓሜዎች ተሰጥተውት ነው:: ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ተረጋግጦ ጥቅማቸውን እንዲያሳኩ ያለመ ነው:: ኅብረ-ብሔራዊ አንድነታቸው ከወቅቱ የፖለቲካ ሥሪት፤ ከዘመኑ የኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ ትስስር አንጻር ተመጣጥኖ እንዲሄድ ለማስቻል ነው::

ከዚህ ቀደም በነበሩ ጊዜያት ብሔር ብሔረሰቦች ከአብሮነት ይልቅ ልዩነት፤ ከመተባበር ይልቅ መነጣጠል፤ ከሚያሰባስቡ ትርክትና እሴቶች ይልቅ በሚከፋፍሉ አጀንዳዎች ላይ እንዲጠመዱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራ ነበር:: የወል ማንነትም የሚባል አይታሰብም:: ከዚያ ይልቅ ተናጠላዊ ማንነት ገዝፎ፣ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እስኪረሱ ድረስ በዓሉ የፖለቲካ አጀንዳ ብቻ ሆኖ ቆይቷል::

ከ2010ዓ.ም መንግሥታዊ ለውጥ ወዲህ ግን መጥፎ አስተሳሰቦች በመልካም ትብብርና በሕብር መጓዝን እንዲያነግቡ ሆነዋል፤ መፈናቀልና አለመረጋጋቶች፣ እልፍ ሲልም ጦርነቶች እዚህም እዚያም መታየታቸውን ከማስቀረት አንጻርም አሉታዊ አስተዋጽኦዎች እንዲበራከቱ አድርጓል:: ሕዝቦች የብዝኃነታቸውን ዓርማ አድምቀው እንዲያሳዩ፣ የውል ሰነዳቸውን እንዲገልጡ፣ ኢትዮጵያዊ መልካቸውን እንዲያሳዩ፣ የትናንት አብሮነታቸው በጽኑ መሠረት ላይ እንዲያኖሩ፣ የዛሬ እውነታቸውን እንዲገልጡና የነገ ሕልምና ተስፋቸውን እንዲያለመልሙ እድል ሰጥቷቸዋል::

ለውጡ ኢትዮጵያ በዘመናት ውስጥ በሁለቱም መልክ እንድትገለጥም ያስቻለ ነው:: ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ብዙ የሕዝብ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ሆነዋል:: ቀደም ሲል እንደ ሀገር ተከታታይ የሚባል ልማት እና የኢኮኖሚ እድገት ቢመጣም እድገቱ የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል፣ የዜጎችን የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያና የእርስ በእርስ ትስስርን ከማጠናከር አንጻር እንብዛም የታየ አልነበረም:: ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትም ተረጋግጧል ለማለት ያስቸግራል:: አብዛኞቹ ልማቶችም በውጪ ዜጎች የሚደረጉ እንጂ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ሲያበረታታ አልታየም:: የብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብት ጠብቋል፤ የመልማት መብታቸውን አረጋግጧል፤ ተጠቃሚነታቸውንም አስፍቷል ለማለት እንዲሁ አስቸጋሪ ነው:: ከለውጡ በኋላ ግን ይህንን ችግር ፈተዋል የተባሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል::

የለውጡ ሥራ ለሕዝብ እውቅና ከመስጠትም የጀመረ ነው:: በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል ኃላፊና የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ የብልፅግና ፓርቲ 5ኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን በማስመልከት ባስተላለፉት መልዕክታቸው፤ ትናንት በሕዝባችን የለውጥ ፍላጎት እና ተራማጅ የለውጥ እሳቤን ባነገቡ ብርቱ መሪዎቻችን ጥረት ታግዘን የጀመርነው የለውጥ ጉዞ ብልፅግና ፓርቲን ወልዷል:: በተመሠረተ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን የዓለም ፈርጥ ምድራዊት ኮከብ ሊያደርጉ የሚችሉ መሠረቶችን ጥሏል ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል::

አክለውም እንዳሉት፤ ለውጥ በመምጣቱ እንደ ሀገር ያልታዩ እምቅ ሀብቶችን እንዲታዩ፣ በአቧራ የተሸፈኑ እልፍ ውበቶች እንዲገለጡና አይደፈሬ የሚመስሉ ተግዳሮቶችን በመጋፈጥ ሀገርን ከብተና ማዳን ተችሏል:: በዚህም በሁላችን ከሁላችን ለሁላችን የሆነች ህብረ-ብሔራዊ አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን መገንባት ችለናል::

**በሌማት ትሩፋትና በአረንጓዴ አሻራውም እንዲሁ የተሰሩ ተግባራት ከሀገር አልፈው ዓለምን ያስደመሙ በመሆናቸው በአህጉር ደረጃም ልምድ ተቀስሞባቸዋል**

ይህንን እውነት የብልፅግና ፓርቲ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ቢቂላ ሁሪሳ (ዶ/ር) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ቃለ ምልልስ ባደረጉበት ወቅት አረጋግጠዋል:: እርሳቸው እንዳሉት፤ ብልፅግና እንዲፈጠር ካደረጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በሀገራችን የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ባለፉት ሥርዓታት በአግባቡ ባለመመለሳቸው ነው:: ኅብረ ብሔራዊ የሆነ ሀገር ለመመሥረት አልተቻለም:: ሀገረ መንግሥቱና ብሔረ መንግሥቱ የነበሩት እጅግ በጣም ፈተና ውስጥ ነው:: የዜጎች መሠረታዊ ጥያቄዎችና መብቶች የእኩልነት፣ የነፃነትና የፍትህ ጥያቄዎች ያልተመለሱበት ጊዜም ነበር:: ሆኖም ሕዝቡ በአደባባይ ወጥቶ ለውጥ ፈላጊነቱን በማሳየቱ ብልፅግና ተወልዶ የእኩልነትን፣ የነፃነትን የሁሉም፣ በሁሉም ከሁሉም የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር የሚቻልበት ላይ እንዲሰራ ሆኗል::

በኅብር የደመቀውን አብሮነት፤ ትክክለኛውን ኅብረ-ብሔራዊ ዴሞክራሲ በተግባር መግለጥ እንዲቻልም ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራም አድርጎታል:: ይህ በመሆኑ ሕዝቡ ከተናጠል ይልቅ በጋራ መቆም ያለውን የላቀ አቅም እንዲያሳይ አድርጓል:: እንደ ሕዝብ ከነጣጣይ ትርክቶች ይልቅ ለአሰባሳቢ ሀገራዊ አብይ ትርክቶች ቦታ እንዲሰጥ፤ እውነተኛ የኅብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ሥርዓቱ ቅኝቱ ኢትዮጵያውያን ማንነታቸውን ከፍ እንዲያደርግ መደላደልንም ፈጥሯል:: የትናንት ስህተትን ማረም ላይ ብቻ ከመታጠር ተወጥቶ የዛሬን ተጨባጭ ሃቅና እውነት መግለጥ ተጀምሯል::

ከትናንት ይልቅ ዛሬ የተሻለ ስለመሆኑ፤ ከዛሬም ደግሞ ነገ በእጅጉ የተሻለ እንደሚሆን በተግባር ወደማሳየቱም ተገብቷል:: ለዚህም አብነት የሚሆኑንን ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን ማንሳት ይቻላል:: የሕዝብ መብት ተከበረ የሚባለው በፍጥነት የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ሲያገኙ በመሆኑ፤ የለውጡ መንግሥት ከጅምሩ ኢትዮጵያ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ፤ መስሪያና መለወጫ እንደሆነች ያሳየበት ተግባር አንዱ እውነቱን ከገለጡት ሥራዎች መካከል ነው:: ለውጡ ሲመጣ በፖለቲካ አመለካከታቸው እና በትግል ስልታቸው ምክንያት ከሀገር የተሰደዱት ሀገራቸው ላይ መጥተው የፈለጉትን እንዲያደርጉ እድል ሰጥቷቸዋል::

ከዚህ በተጓዳኝ አሳሪና ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዘኑ የሕግ ማሕቀፎች እንዲሻሻሉ፣ በአዳዲስ ሕጎች እንዲተኩና አዲስ የሆኑ ሕጎችም እንዲወጡም አስችሏል:: ይህ ደግሞ ከፖለቲካው አንጻር ስናየው አጋር እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ ድርጅቶች ሳይቀሩ መፍትሄ እንዲያገኙና የክልላቸውን ብቻ ሳይሆን የሀገር ውሳኔ ላይ ጭምር እኩል መብት እንዳላቸው እንዲያሳዩ እድል ሰጥቷል:: ስለ ሕዝባቸው ጉዳይም ዝም እንዳይሉ አድርጓቸዋል::

ከለውጡ በኋላ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ኃይልና አቅም አግኝተው ለሕዝቡ ጥቅምና ደህንነት እንዲሟገቱ እድል አግኝተዋል:: በነጻነት ተቀላቅለው ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ እንዲሆኑም ተደርገዋል::

በፖለቲካው ዘርፍ የሕዝብ ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ከሆነባቸው ተግባራት መካከል ሌላው የክልልነት ጥያቄዎች መልስ ማግኘታቸው ነው:: በሞግዚት ይተዳደሩ የነበሩ ክልሎች የራሳቸው መብት ተሰጥቷቸው የራሳቸውን አስተዳዳሪ መርጠው እንዲተዳደሩ ሆነዋል:: የራሳቸውን ሕዝብ ራሳቸው እንዲያስተዳድሩት እድል አግኝተዋል:: በራሳቸው ቋንቋ፤ በራሳቸው ባህልና ወግ እየተመሩም ነው:: በተለይም ከበጀት አንጻር የሚያነሷቸው ጥያቄዎች መፍትሄ ያገኙ ይመስላል:: እንደውም ከዚያም አልፈው በጀት አመንጪ እንዲሆኑም መደላደል ተፈጥሮላቸዋል:: ምክንያቱም በተሰሩ ሪፎርሞች በራሳቸው ሀብት ራሳቸው የሚያዙበትን እድል ተጎናጽፈዋል::

ሌላው ከለውጡ በኋላ ለብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት መከበር የተሰራው ስራ ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ማረጋገጥ ነው:: እንደ ሕዝብ ሰፊውን ድርሻ የሚይዘው አርሶ አደሩ ነው:: ከዚህ አንጻር የሀገር የኢኮኖሚ ምህዋር የሚዘውረው ግብርናው እንደሆነ እንረዳለን:: የአርሶ አደሩ የመልማት መብትን ከማረጋገጠ አንጻር የግብርና ሜካናይዜሽን ላይ የተሰራው ተግባር በቂ ማሳያ ይመስላል:: በክላስተር እንዲያለሙ ሲያደራጃቸው ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን ቆጥበው ምርታማነታቸውን የሚጨምሩበት መሳሪያ ጭምር በማመቻቸት ነው:: ይህ በመሆኑ ሕዝቡ ከሸማችነት ወጥቶ ወደ ሁሉን አቀፍ አምራችነት ተሸጋግሯል:: ኢትዮጵያ ታምርት ተብሎ፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች በስፋት እንዲያመርቱ ሆነዋል:: በምግብ ራስን እንቻል በሚልም ግብርናው ትርፍ አምራችነትን ተጎናጽፏልም::

በሌማት ትሩፋትና በአረንጓዴ አሻራውም እንዲሁ የተሰሩ ተግባራት ከሀገር አልፈው ዓለምን ያስደመሙ በመሆናቸው በአህጉር ደረጃም ልምድ ተቀስሞባቸዋል:: ይህ ብቻም አይደለም ከገበታ ለሸገር እስከ ገበታ ለትውልድ የዘለቁ፤ አሁን ደግሞ መነሻውን አዲስ አበባ አድርጎ እስከ ገጠር ቀበሌዎች የደረሱ የኮሪደር ልማት ሥራዎችም ሀገር እየለማች እንድትቀጥልና ከአደጉት ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ የሚያስችሉ የሕዝብን ጥያቄ የሚመልሱ የለውጡ የኢኮኖሚ ትሩፋቶች ናቸው::

በማህበራዊ ዘርፍም የሕዝቦችን መብት ያረጋገጡ በርካታ ተግባራት ከለውጡ በኋላ ተከናውነዋል:: ይህ ደግሞ ተግባራቱ የዜጋውን ማኅበራዊ ስሪት፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ ሥነልቦናዊ ማንነትና ልዕልና የሚያጎናጽፉ ስለመሆናቸው ራሳችን ምስክርነት የምንሰጥባቸው ናቸው:: የጤና እና የትምህርት ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች በብዛትም በጥራትም መከናወናቸው ጤናማ ዜጋንና የተማረ ማህበረሰብን ከመፍጠር አንጻር የማይተካ ሚና ይኖረዋል:: ይህንን ደግሞ ከለውጡ በኋላ የተመለከትነው እንደሆነ «ትውልድ ለሀገር» የትምህርት ቤት ግንባታዎችን ብቻ በመጥቀስ መናገር ይቻላል::

የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት መረጋገጥ በማህበራዊ ዘርፉ ያለው ጠቀሜታ ከሌላም አቅጣጫ የሚታይ ነው:: ይህም በዓላቱን ከማክበርና እንዲታሰብ ከማድረግ አንጻር ያለው ጥቅም ሲሆን፤ በበዓሉ መከበር አማካኝነት የሀገር እሳቤ እንዲያቆጠቁጥ ይሆናል፤ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን የትናንት የበዛ የጋራ ታሪክ፣ መንገድና ገድላቸው እንዲተዋወቁም እድል ይፈጥራል:: በተመሳሳይ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በኢትዮጵያ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚናና ድርሻ ተገንዝበው እንዲሰሩ ያደርጋል:: ኢትዮጵያዊያን እንደ ሀገር የወደፊትን ተልሞ እና ተባብሮ የመሥራት አቅም ያላቸው መሆናቸውንም እንዲያረጋግጡ መደላደልን የሚፈጥር ነው::

ይሄ ደግሞ ነገ ለልጆቻችን የተሻለ እድል ይፈጥራል:: ከትናንት ቁርሾና ንትርክ ነጻ የመውጣትን እድል ያጎናጽፋል፤ ከመነጠል ይልቅ በኅብር የመቆማችንን ኃያልነት ያሳያል:: ከሁሉም በላይ ዛሬን መሥራት፤ ዛሬን ዋጋ መክፈል፤ ዛሬን በንጹህ ልብ ሆኖ ቁጭ ብሎ መነጋገርን፤ ዛሬን ስለ ትናንት ሳይሆን ስለ መጪው እያሰላሰልን የተሻለ ነገርን የመተለም ልዕልናን ከእኛ ጋር ያደርጋል::

ስለሆነም ይህንን እድል የመጠቀሙ ሁኔታ የሁሉም ዜጋ ነውና ማንነታችንን ይዘን ኢትዮጵያዊነታችንን ከፍ ማድረግ፤ አንድነታችንን አጠንክረን ኅብረ-ብሔራዊነታችንን መግለጥ፤ ታሪካችንን ከተዛባ መስመሩ አውጥተን በትክክለኛና እውነተኛው ትርክት ማነጽና የጋራችን የሆነውን ሃቅ ማኖር ይጠበቅብናል በማለት ሃሳቤን ቋጨሁ:: ሰላም!!

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## አሲዳማ አፈርን በኖራ አክሞ ምርታማነትን ማሳደግ ያስቻለው ተሞክሮ

**ኢያሱ መሰለ**

የኢትዮጵያን የግብርና ምርታማነትና ምርታማነትን ከሚፈታተኑ ችግሮች አንዱ የአፈር አሲዳማነት መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ አሁን በሀገሪቱ ከሚታረሰው መሬት ወደ ሰባት ሚሊዮን ሄክታሩ ወይም 43 ከመቶው የሚሆነው በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ሶስት ሚሊዮን ሄክታሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ በአሲዳማነት የተጠቃ መሆኑ ይገለጻል፡፡ ይህ ችግር እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ትኩረት ሳይሰጠው በመቆየቱም በምርታማነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲፈጥር መቆየቱን የግብርና ባለሙያዎች ያመለክታሉ፡፡

በዚህ አሲዳማነት ከተጠቃው መሬት ሰባት ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነውን ብቻ በኖራ የማከም ስራ ቢሰራ ምርትና ምርታማነትን በሃምሳ በመቶ ማሳደግ እንደሚቻልም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ኖራን ብቻ በመጠቀም ምርታማነትን ከ10 ኩንታል በሄክታር ወደ 40 እና 50 ኩንታል ማሳደግ እንደሚቻልም ይጠቅሳሉ፡፡

ግብርናው በምግብ ራስን ከመቻል አልፎ በኢኮኖሚ እድገቱ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ሀገራዊ የግብርና ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ኩታ ገጠም እርሻ ፣ የበጋ ስንዴ፣ የከተማ ግብርና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በአሲድ የተጠቃ መሬትን በኖራ እያከሙ የምርታማነት ደረጃን ማሳደጉም ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ ነው፤ በዚህም ምርት አልሰጥ ብለው የቆየ መሬት ምርታማ እየሆነ መምጣቱንና አስገራሚ ለውጦች የተመዘገቡ መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡

በአሲድ የተጠቁ መሬቶችን በኖራ እያከሙ ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ከሚሰራባቸው ክልሎች አንዱ የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ነው፡፡ በዘንድሮው የመኸር ወቅት በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሸዋ ዞን፤ ወልመራ ወረዳ፤ ሀሮ ቦኪ ቀበሌ ልዩ ስሙ ተሴ በረንዳ በሚባል መንደር በኖራ በታከመ 853 ሄክታር መሬት ላይ የተዘራ የገብስ ሰብል የምርታማነት ደረጃ ከእጥፍ በላይ ማደግ ችሏል፡፡

በክልሉ አፈ-ጉባኤ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራህማን የተመራ ቡድንም በቅርቡ በሥፍራው ተገኝቶ የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ ዲዳ ጉደታ እንደገለፁት፤ በኦሮሚያ ክልል በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ መሬት ከሚገኝባቸው አካባቢዎች አንዱ የምእራብ ሸዋ ዞን ነው፡፡ በዘንድሮው የመኸር ወቅት 108 ሺህ 886 ሄክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች የተሸፈነ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በአሲዳማነት የተጎዳና ለረዥም ጊዜ የሚፈለገውን ምርት መስጠት ያልቻለ መሬት ይገኝበታል፡፡

የዞኑ አስተዳዳሪ እንዳሉት፤ የክልሉ መንግሥት አሲዳማ አፈርን በኖራ የማከም ንቅናቄ ውስጥ መግባቱን ተከትሎ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል የኖራ ፋብሪካ በዞኑ እንዲገነባ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በአፈር አሲዳማነት የተጎዳ መሬትን በኖራ በማከም የምርታማነት መጠኑ እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል፡፡

በ2016/17 የመኸር ወቅት በአሲዳማነት የተጠቃ ከ40 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በኖራ አክሞ የተለያዩ አዝርዕቶችን በመዝራት የዞኑን ምርታማነት ማሳደግ መቻሉን አቶ ዳዲ አስታውቀዋል፡፡ የአፈር አሲዳማነቱን በኖራ በማከመም አበረታች ውጤት እየተገኘ ስለመሆኑ ያመላክታሉ፡፡

የወልመራ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪና የእርሻና መሬት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ተሾመም በዘንድሮው የመኸር ወቅት ከሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ጋር በመተባበርና በኦሮሚያ ግብርና ቢሮና በዞኑ ድጋፍ በአሲድ የተጠቃ መሬትን በኖራ በማከም ምርታማነትን ማሳደግ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

በ853 ሄክታር መሬት ላይ የተደራጁ 173 አርሶ አደሮች በኩታ ገጠም እርሻ መሬታቸውን በኖራ አክመው በገብስ ዘር መሸፈናቸውን አቶ ደሳለኝ ጠቅሰው፣ ውጤቱም አስደሳች መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአካባቢው መሬት በአሲዳማነት በመጠቃቱ ምክንያት ምርት የመስጠት አቅሙ ተዳክሞ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ደሳለኝ፤ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ ባደረጋቸው ማሻሻያዎች ምርታማነት እየጨመረ እንደሚገኝና የአካባቢው አርሶ አደሮችም መሬታቸውን በኖራ የማከሙን ቴክኖሎጂ እየተጠቀሙ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

በአሲድ የተጠቁ መሬቶች ከዚህ በፊት ማዳበሪያ ቢደረግላቸውም የሚሰጡት ምርት አነስተኛ ነበር ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ በኖራ እያከሙ መዝራት ከተጀመረ ከአስር ዓመታት ወዲህ ግን አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል፡፡



**በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሸዋ ዞን ተግባራዊ የተደረገው መሬትን በኖራ እያከሙ ምርታማነትን የማሳደጉና የበጋ ስንዴን በከርሰ ምድር ውሃ የማልማቱ ሥራ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ እየወሰደ ያለውን ርምጃ ያመለክታል**

ከወረዳው በቅርበት የሚገኘው የጉደር ኖራ ፋብሪካም መሬቱን ለማከም የሚያስፈልገውን የኖራ ግብዓት ከማምረት አንጻር ለግብርናው ምርታማነት አስተዋጽኦው ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ መሬቱን በማከሙ ሂደትም ቢያንስ አንድ ሺ 700 ጆንያ/ቁምጣ ጆንያ/ ኖራ በ853 ሄክታር መሬት ላይ በመጠቀም ውጤት ማምጣት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

አርሶ አደሮች በዚህ ልክ በክላስተር ተደራጅተው መሬታቸውን በኖራ በማከምና የግብርና ፓኬጆችን በሙሉ በመጠቀም ያገኙት ውጤት በቀጣይም የባለሙያዎችን ምክር እንዲሰሙና ለተሻለ ውጤት እንዲተጉ እንደሚያደርጋቸው ተናግረዋል ፡፡

በወልመራ ወረዳ በተጎበኘው የገብስ አዝመራ፤ አርሶ አደሮች በኖራ በታከመው መሬት ላይ ኩታ ገጠም እርሻንና ምርጥ-ዘርን በመጠቀም፣ በመስመር በመዘራትና የግብርና ፓኬጆችን ሙሉ ለሙሉ በመጠቀም በሄክታር 70 ኩንታል የሚገመት ምርት ማግኘት መቻላቸውን አስረድተዋል፡፡

የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ ዲዳ ጉደታ በአምቦ ከተማ አካባቢ አርሶ አደሩ የሚያመርተውን የገብስ ምርት ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት እንዲሆን በማሰብ ግዙፍ የቢራ ፋብሪካ ግንባታ እየተጠናቀቀ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በኖራ በሚታከመው መሬት ላይ የሚመረተው የቢራ ገብስ ምርታማነት እንዲጨምርም አርሶ አደሩ በክላስተር የማረስ ልምዱን አዳብሮና አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ኢንዱስትሪዎችን በመመገብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን የሚያረጋግጥበት እድል ተፈጥሮለታል ብለዋል፡፡

ማምረት ብቻ ሳይሆን የደረሱ ሰብሎችን በሰዓቱ ሰብስቦ ወደ ጎተራ ማስገባትም የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ የሚያደርግ ሌላው ሥራ ነው ያሉት የዞኑ አስተዳዳሪ፤ እስከ አሁንም ከደረሱ ሰብሎች ውስጥ 40 በመቶ የሚሆነው ሰብል መሰብሰቡን ይገልጻሉ፡፡ የደረሱ ሰብሎችን በማሽኖች የመሰብሰብ ልምድ እንዳልነበር ገልጸው፤ በአሁኑ ሰዓት እንደ ገብስና ስንዴ የመሳሳሉት የደረሱ ሰብሎች በማሽኖች እንዲሰበሰቡ እየተደረገ ነው ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

በምዕራብ ሸዋ ዞን ወልመራ ወረዳ የሀሮ ቦኪ ቀበሌ ነዋሪው አርሶ አደር መልካ ጆቴ እንደሚሉት፤ ከ10 ዓመት በፊት የአካባቢው አርሶ አደሮች ስለአሲዳማ መሬቶች ምንነት አያውቁም ነበር፡፡ የወረዳው ግብርና ቢሮ በሚመራው ፕሮግራም አማካኝነት የግብርና ባለሙያዎች ለአካባቢው አርሶ አደሮች ተገቢውን ግንዛቤ በማስጨበጥ ስለአሲዳማ መሬቶችና በኖራ እየታከሙ ምርታማ ስለሚሆኑበት ሁኔታ አስተምረዋል፡፡ በተሰጠው ስልጠና መሰረትም መሬቱ በኖራ የተጠቃ ስለመሆኑ አስቀድሞ ይመረመራል፤ አሲዳማነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በኖራ የማከሙ ስራ ይከናወናል ፡፡

መሬታችን ከ30 አመታት በፊት ጀምሮ ምርታማ አልነበረም ያሉት አርሶ አደር መልካ፤ እህል ተዘርቶ ሸማማ የሚባል ነገር እንደሚያበቅልና እሱም ቢሆን በደንብ ተመችቶት እንደማያድግ ገልጸዋል፡፡ በወቅቱ ከሚዘራው ነጭ-ገብስ ከሄክታር ከአምስት እና ስድስት ጆንያ በላይ እንደማይገኝ ጠቅሰው፤ የልማት ሠራተኞች ምስጋና ይግባቸውና በዘንድሮው ዓመት ከወረዳው ግብርና ቢሮ ጋር በመነጋገር መሬቱን አስመርምረን አስፈላጊውን የኖራ መጠን በመጠቀም ይህን የመሰለ ምርት ማግኘት ችለናል ብለዋል፡፡ «መሬት እንደሰው ይታመማል፤ ታመመ ብለንም አንተወውም፤ የሚያስፈልገውን ህክምና አድርገንለት ምርታማ እንዲሆን እናስችለዋለን እንጂ»ይላሉ፡፡

በኖራ ታክሞ የተዘራው ገብስ አዝመራ ባለፉት ዓመታት ከነበረው ጋር ሲነጻፀር እጅግ በጣም አስደሳች ነው ያሉት አቶ መልካ ፤ አርሶ አደሩ እንደከዚህ ቀደሙ በፈለገው መንገድ መጓዝ ሳይኖርበት የዘርፉ ሙያተኞች የሚሰጡትን ምክር ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡፡ በዚህ ቴክኖሎጂ ከዚህ በኋላ በየዓመቱ ጤፍም ይሁን ሌሎች ሰብሎችን የማምረት ተስፋ እንደተገኘም ተናግረዋል፡፡

በጉብኝት መርሃ-ግብሩ ላይ የተገኙት የጨፌ ኦሮሚያ አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራህማን በበኩላቸው፤ መንግሥት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ግብርናው ከምግብ ፍጆታ ያለፈ ምርት በማምረት ለገበያ ማቅረብ እንዲችልም ከተለምዷዊ አሠራር ተላቆ በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ የእርሻ መሬቶች ሁሉ ጾማቸውን እንዳያድሩ እና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉም እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ምርታማነትን ለማሳደግ ያሉትን አቅሞች በሙሉ መጠቀም እንዲቻልም አቅጣጫ ተይዞ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ሸዋ ዞን ተግባራዊ የተደረገው መሬትን በኖራ እያከሙ ምርታማነትን የማሳደጉና የበጋ ስንዴን በከርሰ ምድር ውሃ የማልማቱ ሥራ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ እየወሰደ ያለውን ርምጃ ያመለክታል፡፡ በርትቶ መሥራት ከተቻለ ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችል ትልቅ ሀብትና አቅም እንዳለም የታየበት አጋጣሚ ብዙ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በወልመራ ወረዳ የታየው የቢራ ገብስ ምርታማነትም ለእዚህ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ለቢራ ፋብሪካዎች ግብዓት የሚሆን የቢራ ገብስ ከውጭ ይመጣ እንደነበር ያስታወሱት ወይዘሮ ሰዓዳ፤ በአሲድ የተጠቃውን መሬታችንን በመኖራ በማከምና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተገኘው ውጤት ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት መሆን የሚችል ምርት ማምረት እንደምንችል ያየንበት ነው ብለዋል፡፡

በከፍተኛ ደረጃ በአሲድ የተጠቃውን እና ምርት ለመስጠት ይቸገር የነበረውን መሬት በኖራ በማከም ከሚገመተው በላይ ምርታማነትን ማሳደግ መቻሉ ለአርሶ አደሩ ተስፋ የሰጠ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ምርት አይሠጥም ብለን ችላ ያልነው መሬት ላይ ትኩረት ሰጥተን አማራጮችን ሁሉ ተጠቅምን የምንሰራ ከሆነ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል አይተናል ሲሉ ተናግረዋል ፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የግብርና ባለሙያዎች ቁርጠኛ ሆነው ከአርሶ አደሩ ጎን ከቆሙ አግሮ ኢኮሎጂውን በጠበቀ መንገድ ያለውን መሬት በአግባቡ በመጠቀም ከተሰራበት የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፎ ለገበያ የሚተርፍ ምርት ማምረት ይቻላል፡፡ አርሶ አደሩ የመንግሥትን የልማት አቅጣጫዎች ከተከተለና የባለሙያዎችን ምክር ተቀብሎ ጥቅም ላይ ካዋለ አትራፊ እንጂ ተጎጂ እንደማይሆን በኖራ የታከመው አሲዳማ መሬት ምስክር ነው ፡፡

በቀጣይም ምርታማነትን ለማሳደግ መንግሥት የሚነድፋቸውን የሥራ አቅጣጫዎች አርሶ አደሩ በግብርና ባለሙያዎች እየታገዘ እንዲተገበራቸው ወይዘሮ ሰዓዳ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹አምቦ ሰላሟን እያስጠበቀች፤ ልማቷን እያስቀጠለች ያለች ከተማ ናት››

-አቶ ተስፋዬ ደገፋ የአምቦ ከተማ ምክትል ከንቲባ

ኢያሱ መሰለ

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውክልና ያላት ሀገር እንደመሆኗ በጉያዋ ያቀፈቻቸውን ልጆቿን ያማከለ መልክ እንዲኖራት የተለያዩ ተጋድሎዎች ተደርገዋል፡፡ ከተለያዩ የትግል ምዕራፎች ውስጥም ስመ ጥር ከሆኑ የሀገሪቱ ከተሞች መካከልም አምቦ ከተማ ተጠቃሽ ነች፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ገዢና ጨቋኝ ናቸው የሚላቸውን ሥርዓቶች ከጫንቃው ላይ ለመጣል ባደረገው ተጋድሎ ፋና-ወጊ ከነበሩት እንዲሁም የለውጥ እርሾ ከሚጣልባቸው እና የትግል ማዕከል ከሆኑ የክልሉ ከተሞች ውስጥ አምቦ ግንባር ቀደም ከተማ ነች፡፡

አምቦና አካባቢዋ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ጭቆና የሚሞግቱ ጉምቱ ፖለቲከኞች የሚወጡባት፣ ስለነጻነት የሚያቀነቅኑ ስመጥር ድምጻውያን የሚፈልቁባትም ነች፡፡ ከዚህ ከተማ የሚነሳው የነጻነት እና የእኩልነት ድምጽ ምቾት የሚነሳቸው የየሥርዓቱ ገዢዎችም ከተማዋ በልማት እንድታድግ ከማገዝ ይልቅ መቀጣጫ እንድትሆን በሚመስል መልኩ የልማት ተጠቃሚ እንዳትሆን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ አምቦ ዛሬ በተለይም ከስድስት ዓመት ወዲህ ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ፊቷን ወደ ልማት አዙራለች፤ በዚህም መሻሻሎችን አሳይታለች፡፡ 19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በክልል ደረጃ እንድታስተደናግድም ታጭታለች፡፡ እኛም በዛሬው የእንግዳ አምድ ዝግጅታችን አምቦ ከተማን ልንቃኝ ወደናል፡፡ ከተማዋ በሰላምና ጸጥታ፣ በከተማ ግብርና ፣ በኮሪደር ልማት፣ በሥራ እድል ፈጠራ እና በሌሎችም ጉዳዮች እያደረገች ያለችውን የሥራ እንቅስቃሴና ያስመዘገበችውን ለውጥ በተመለከተ ከከተማዋ ምክትል ከንቲባ አቶ ተስፋዬ ደገፋ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- የአምቦ ከተማ እና አካባቢው በኦሮሞ ሕዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የመሆኑን ያህል በተለይም ባለፉት ሥርዓቶች በልማት ተጠቃሚ አልነበረም ይባላል፤ ለምንድን ነው?**

**አቶ ተስፋዬ ደገፋ፡-** አመሰግናለሁ! ሁላችሁም እንደምታውቁት የአምቦ ከተማና የአካባቢው ማህበረሰብ ጫንቃው ላይ የተጫነውን ጨቋኝ ሥርዓት ከስሩ ነቅሎ ለመጣል ለረዥም ዓመታት በትግል ላይ ያሳለፈ ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ዋና ትኩረቱ የነበረው የጭቆና ሥርዓትን ገርስሶ እኩልነት ፣ ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማስፈን ስለነበር እምብዛም ወደ ልማት ሥራዎች የገባበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ከሌሎች የኦሮሞ ማህበረሰቦች እንዲሁም ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመተባበር ከፍተኛ ትግል አድርጎ ጨቋኝ ሥርዓትን በመጣል፤ አሁን የታየው ለውጥ እንዲመጣ የራሱን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ የተጠመደ ነበር፡፡

በዚሁ መሰረት ከአምስት እና ስድስት ዓመታት በፊት የመጣው ለውጥ ለአምቦ ከተማም ይሁን ለመላው ኢትዮጵያ መልካም እድል ይዞ እንደመጣ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ መላው የምዕራብ ሸዋም ይሁኑ የአምቦ ከተማ ነዋሪዎች ለውጡ ያመጣላቸውን መልካም አጋጣሚዎች ተጠቅመው ፊታቸውን ወደ ልማት አዙረዋል፡፡ የአምቦ ከተማም በአሁኑ ሰዓት የተገኘውን ለውጥ እንደጥሩ አጋጣሚ ተጠቅማ በልማት ሥራዎች ላይ ተጠምዳለች፡፡ በዚህም የአካባቢውንና የከተማውን ገጽታ የቀየሩ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛል፡፡

የፌዴራል እና የክልሉ መንግሥትም ለከተማዋ ልማትና እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከተማ አስተዳደሩም በበኩሉ ትልቅ በጀት በመበጀትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የሚሰራቸው ሰፋፊ የልማት ፕሮጀክቶች አሉ፤ አምቦ ከተማ ከነበሩባት የመሰረተ ልማት ችግሮች አንዱ መንገድ ነበር፤ አሁን የመንገድ ጥያቄዋን ለመመለስ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ለምሳሌ የፌዴራል መንግሥትን ብንመለከት በአምቦ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የአስፋልት መንገድ እየሠራ ይገኛል፡፡ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትም እንዲሁ ከአሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በማሠራት ላይ ይገኛል፡፡ የፌዴራል መንግሥትና የኦሮሚያ ክልል ከሚያሠሩት የመንገድ ግንባታ በተጨማሪ የአምቦ ከተማ አስተዳደር ትልቅ በጀት በመመደብና ህብረተሰቡን በማሳተፍ ከተማዋን በውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለማስተሳሰር በስፋት እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ የሥራ ሂደት በርካታ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተሠርተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ አሁንም በግንባታ ላይ ያሉ አሉ፡፡

እንደሚታወቀው ከአዲስ አበባ ከተማ ተነስቶ አምቦ ከተማን በማቋረጥ ወደ ወሊጋ የሚዘልቀው መንገድ ቀደም ሲል አንድ ብቻ ነበር፤ በዚህም ላይ ጠባብ ነበር፡፡ አሁን ከአንድ በላይ የሆኑ የመንገድ አማራጮችን ገንብቶ ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የአምቦ ከተማ የፌዴራል መንግሥት፣ የክልሉ መንግሥት፣ ከተማ አስተዳደሩና ሕዝቡ በሚያደርጉት ርብርብ የመንገድ መሰረት ልማት ጥያቄዋ እየተመለሰ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋ ከንጹህ መጠጥ ውሃ ፣ ከመብራትና ከመኖሪያ ቤት አቅርቦት አንጻር ምን ትመስላለች?**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** የከተማዋ ነዋሪዎችን የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ ማሟላት ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እንደ ከተማ የሚነሱ የውሃ አቅርቦት ጥያቄዎች የሉም፡፡ የመብራት ፍላጎት ጥያቄዎችም በተመሳሳይ መንገድ ተመልሰዋል፤ ሌላው ቀርቶ የቴሌኮም ኔትወርክ ችግር አይስተዋልም፡፡ በከተማው የመኖሪያ ቤት እጥረት ችግር ግን አለ፤ በአሁኑ ሰዓት የቁጠባ ቤቶችን በመገንባት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የቀበሌ ቤቶችንም በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል አሰራር ዘርግተን ችግሩን ለመፍታት እየጣርን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል ምን ያህል አቅም አለ? በተያዘው በጀት ዓመትስ ለምን ያህል ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታስቧል?**

**አቶ ተስፋዬ፡-**ከተማአስተዳደሩበሚፈጥራቸው ምቹ ሁኔታዎች ህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆን ይፈለጋል። ከዚህ አንጻር የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። እንደሚታወቀው አምቦ ከተማ በስተምዕራብ ፊንፊኔ በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝና ወደ ወለጋ፣ ወሊሶና ሌሎችም ከተሞች መግቢያና መውጫ ኮሪደር ያላት በመሆኑ ለንግድ፣ ለሥራ ፍለጋ፣ ለተመቻቸ ኑሮና ለተለያዩ ጉዳዮች ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ በርካታ ሰዎች ይኖሩባታል። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ብዛቷ በየጊዜው ያድጋል፤ የሥራ ፈላጊው ቁጥርም በዚያው ልክ ይጨምራል። በመሆኑም ያለው ሥራ ፈላጊዎች ቁጥር እና ያለው የሥራ እድል አሁንም በሚፈለገው ልክ ተጣጥሟል ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ባለሀብቶችን በማሳተፍ ጭምር የከተማው አቅም በሚፈቅደው ልክ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ትልልቅ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡ እንደሚታወቀው የሥራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረውና ለእድገታችንም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ የሚታመነው ኢንቨስትመንት ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ባለሀብቶች ወደ ከተማዋ እየመጡ ኢንቨስት እንዲያደርጉ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ባለሀብቶች ወደ አምቦ ከተማ መጥተው ኢንቨስት ማድረግ ይቅርና የነበሩት ራሱ ከተማውን ትተው ወደ ሌሎች አካባቢዎች የሚሄዱ ነበሩ፡፡ ከተማቸውን እንዳያለሙ ያደረጋቸው አንዱ ምክንያት የሰላም ጉዳይ ነበር፡፡

አሁን አምቦ ሰላሟን እያስጠበቀች፤ ልማቷን እያስቀጠለች ያለች ከተማ ሆናለች፤ በዚህ የተነሳ ኢንቨስተሮች ወደ ከተማዋ እየተሳቡ መጥተዋል። በርካታ ባለሀብቶች በልማት ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ በመሆኑም የሥራ እድል እየተፈጠረ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ቢያንስ ከ195 በላይ ኢንቨስተሮች መሬት ወስደው በሥራ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ አብዛኛዎቹም ከ70 በመቶ በላይ ቅድመ ዝግጅትና የግንባታ ሥራዎችን ሠርተው በአጭር ጊዜ ወደ ሙሉ ሥራቸው የሚገቡ እንደሆነ ይጠበቃል። እነዚህ ወደ ርራ ሲገቡ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል የሚፈጥሩ ይሆናሉ፡፡ የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ በተያዘው ዓመት ብቻ በከተማዋ 20ሺ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል፡፡ የሥራ ዕድል ፈጠራውን በተለያዩ የሥራ መስኮች ተግባራዊ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎችም በየጊዜው እየተገመገሙ ይገኛል፡፡ እቅዱ ግቡን እንዲመታም የባለሀብቱ ተሳትፎና የአመራሩ ቁርጠኝነት ወሳኝ ጉዳይ በመሆናቸው ሀብትን፣ ገንዘብን እና ጉልበትን በማቀናጀት የሥራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- የልማት መሠረቱ ሰላም ነው፤ የአምቦ ከተማ የሰላም ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት አሁን የታየው ለውጥ በሕዝቡ መስዋዕትነት የተገኘ እንደመሆኑ ለውጡን ሕዝቡ ራሱ እየጠበቀው ይገኛል፡፡ ህብረተሰቡ ለውጡን የማስጠበቅ ወይም የማስቀጠል ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበትም ያምናል። ሥርዓቱን ያመጣው ራሱ በመሆኑም ይጠብቀዋል፤ እየጠበቀውም ይገኛል፡፡ ሕዝቡ ሰላሙን የመጠበቅ ከፍተኛ ፍላጎትም አለው፡፡ ይህ የሕዝቡ የሰላም ፍላጎት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ደግሞ በእኛ በኩል መሥራት የሚጠበቅብንን እንሠራለን። ሰዎች የሚያቀርቧቸው የሰላም ጥያቄያቸው ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡ በዚሁ መሰረት ከሰፈር ጀምሮ እስከ ከተማ መዋቅር ድረስ ህብረተሰቡን እና የጸጥታ አካሉን የማቀናጀት፣ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራዎች በአመራሩ በኩል ይሠራሉ፡፡

የማህበረሰብ ፖሊስ፣ የከተማ ሚሊሻ፣ የሥርዓቱ ጋሻዎች የሚባሉት የየአካባቢው ሥርዓት አስጠባቂዎች (ሲርና ጋቸና)፣ የአምቦ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ ፌዴራል ተቋማት የተመደቡ የፌዴራል ፖሊሶች፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እንዲሁም የየአካባቢው ማህበረሰብ ተወካዮች የከተማውን ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር የየራሳቸውን ሥራ ይሠራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሁሉም የጸጥታ አካላት የተውጣጣ አደረጃጀት በመፍጠር ሁሌም በከተማውና በአካባቢው ሰላም ጉዳይ ምክክሮችና ውይይቶች ይደረጋሉ፤ በመድረኩ አሠራሮች ይገመገማሉ፤ በሰላምና ጸጥታ ጉዳይ መሠራት ስላለባቸው ነገሮች የጋራ አቅጣጫዎችም

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹አምቦ ሰላሟን እያስጠበቀች፤ ልማቷን እያስቀጠለች ያለች ከተማ ነች››

**-አቶ ተስፋዬ ደገፋ የአምቦ ከተማ ምክትል ከንቲባ**

ኢያሱ መሰለ

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውክልና ያላት ሀገር እንደመሆኗ በጉያዋ ያቀፈቻቸውን ልጆቿን ያማከለ መልክ እንዲኖራት የተለያዩ ተጋድሎዎች ተደርገዋል፡፡ ከተለያዩ የትግል ምዕራፎች ውስጥም ስመ ጥር ከሆኑ የሀገሪቱ ከተሞች መካከልም አምቦ ከተማ ተጠቃሽ ነች፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ገዢና ጨቋኝ ናቸው የሚላቸውን ሥርዓቶች ከጫንቃው ላይ ለመጣል ባደረገው ተጋድሎ ፋና-ወጊ ከነበሩት እንዲሁም የለውጥ እርሾ ከሚጣልባቸው እና የትግል ማዕከል ከሆኑ የክልሉ ከተሞች ውስጥ አምቦ ግንባር ቀደም ከተማ ነች፡፡

አምቦና አካባቢዋ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ጭቆና የሚሞግቱ ጉምቱ ፖለቲከኞች የሚወጡባት፣ ስለነጻነት የሚያቀነቅኑ ስመጥር ድምጻውያን የሚፈልቁባትም ነች፡፡ ከዚህ ከተማ የሚነሳው የነጻነት እና የእኩልነት ድምጽ ምቾት የሚነሳቸው የየሥርዓቱ ገዢዎችም ከተማዋ በልማት እንድታድግ ከማገዝ ይልቅ መቀጣጫ እንድትሆን በሚመስል መልኩ የልማት ተጠቃሚ እንዳትሆን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ አምቦ ዛሬ በተለይም ከስድስት ዓመት ወዲህ ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ፊቷን ወደ ልማት አዙራለች፤ በዚህም መሻሻሎችን አሳይታለች፡፡ 19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በክልል ደረጃ እንድታስተደናግድም ታጭታለች፡፡ እኛም በዛሬው የእንግዳ አምድ ዝግጅታችን አምቦ ከተማን ልንቃኝ ወደናል፡፡ ከተማዋ በሰላምና ጸጥታ፣ በከተማ ግብርና ፣ በኮሪደር ልማት፣ በሥራ እድል ፈጠራ እና በሌሎችም ጉዳዮች እያደረገች ያለችውን የሥራ እንቅስቃሴና ያስመዘገበችውን ለውጥ በተመለከተ ከከተማዋ ምክትል ከንቲባ አቶ ተስፋዬ ደገፋ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- የአምቦ ከተማ እና አካባቢው በኦሮሞ ሕዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የመሆኑን ያህል በተለይም ባለፉት ሥርዓቶች በልማት ተጠቃሚ አልነበረም ይባላል፤ ለምንድን ነው?**

**አቶ ተስፋዬ ደገፋ፡-** አመሰግናለሁ! ሁላችሁም እንደምታውቁት የአምቦ ከተማና የአካባቢው ማህበረሰብ ጫንቃው ላይ የተጫነውን ጨቋኝ ሥርዓት ከስሩ ነቅሎ ለመጣል ለረዥም ዓመታት በትግል ላይ ያሳለፈ ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ዋና ትኩረቱ የነበረው የጭቆና ሥርዓትን ገርስሶ እኩልነት ፤ ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማስፈን ስለነበር እምብዛም ወደ ልማት ሥራዎች የገባበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ከሌሎች የኦሮሞ ማህበረሰቦች እንዲሁም ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመተባበር ከፍተኛ ትግል አድርጎ ጨቋኝ ሥርዓትን በመጣል፤ አሁን የታየው ለውጥ እንዲመጣ የራሱን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ የተጠመደ ነበር፡፡

በዚሁ መሰረት ከአምስት እና ስድስት ዓመታት በፊት የመጣው ለውጥ ለአምቦ ከተማም ይሁን ለመላው ኢትዮጵያ መልካም እድል ይዞ እንደመጣ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እንደሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ መላው የምዕራብ ሸዋም ይሁኑ የአምቦ ከተማ ነዋሪዎች ለውጡ ያመጣላቸውን መልካም አጋጣሚዎች ተጠቅመው ፊታቸውን ወደ ልማት አዙረዋል፡፡ የአምቦ ከተማም በአሁኑ ሰዓት የተገኘውን ለውጥ እንደጥሩ አጋጣሚ ተጠቅማ በልማት ሥራዎች ላይ ተጠምዳለች፡፡ በዚህም የአካባቢውንና የከተማውን ገጽታ የቀየሩ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛል፡፡

የፌዴራል እና የክልሉ መንግሥትም ለከተማዋ ልማትና እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከተማ አስተዳደሩም በበኩሉ ትልቅ በጀት በመበጀትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የሚሰራቸው ሰፋፊ የልማት ፕሮጀክቶች አሉ፤ አምቦ ከተማ ከነበሩባት የመሰረተ ልማት ችግሮች አንዱ መንገድ ነበር፤ አሁን የመንገድ ጥያቄዋን ለመመለስ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ለምሳሌ የፌዴራል መንግሥትን ብንመለከት በአምቦ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የአስፋልት መንገድ እየሠራ ይገኛል፡፡ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትም እንዲሁ ከአሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በማሠራት ላይ ይገኛል፡፡ የፌዴራል መንግሥትና የኦሮሚያ ክልል ከሚያሠሩት የመንገድ ግንባታ በተጨማሪ የአምቦ ከተማ አስተዳደር ትልቅ በጀት በመመደብና ህብረተሰቡን በማሳተፍ ከተማዋን በውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለማስተሳሰር በስፋት እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ የሥራ ሂደት በርካታ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተሠርተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ አሁንም በግንባታ ላይ ያሉ አሉ፡፡

እንደሚታወቀው ከአዲስ አበባ ከተማ ተነስቶ አምቦ ከተማን በማቋረጥ ወደ ወለጋ የሚዘልቀው መንገድ ቀደም ሲል አንድ ብቻ ነበር፤ በዚህም ላይ ጠባብ ነበር፡፡ አሁን ከአንድ በላይ የሆኑ የመንገድ አማራጮችን ገንብቶ ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የአምቦ ከተማ የፌዴራል መንግሥት፣ የክልሉ መንግሥት፣ ከተማ አስተዳደሩና ሕዝቡ በሚያደርጉት ርብርብ የመንገድ መሰረት ልማት ጥያቄዋ እየተመለሰ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋ ከንጹህ መጠጥ ውሃ ፣ ከመብራትና ከመኖሪያ ቤት አቅርቦት አንጻር ምን ትመስላለች?**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** የከተማዋ ነዋሪዎችን የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ ማሟላት ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እንደ ከተማ የሚነሱ የውሃ አቅርቦት ጥያቄዎች የሉም፡፡ የመብራት ፍላጎት ጥያቄዎችም በተመሳሳይ መንገድ ተመልሰዋል፤ ሌላው ቀርቶ የቴሌኮም ኔትወርክ ችግር አይስተዋልም፡፡ በከተማው የመኖሪያ ቤት እጥረት ችግር ግን አለ፤ በአሁኑ ሰዓት የቁጠባ ቤቶችን በመገንባት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የቀበሌ ቤቶችንም በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል አሰራር ዘርግተን ችግሩን ለመፍታት እየጣርን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል ምን ያህል አቅም አለ? በተያዘው በጀት ዓመትስ ለምን ያህል ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታስቧል?**

**አቶ ተስፋዬ፡-**ከተማአስተዳደሩበሚፈጥራቸው ምቹ ሁኔታዎች ህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆን ይፈለጋል። ከዚህ አንጻር የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። እንደሚታወቀው አምቦ ከተማ በስተምዕራብ ፊንፊኔ በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝና ወደ ወለጋ፣ ወሊሶና ሌሎችም ከተሞች መግቢያና መውጫ ኮሪደር ያላት በመሆኑ ለንግድ፣ ለሥራ ፍለጋ፣ ለተመቻቸ ኑሮና ለተለያዩ ጉዳዮች ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ በርካታ ሰዎች ይኖሩባታል። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ብዛቷ በየጊዜው ያድጋል፤ የሥራ ፈላጊው ቁጥርም በዚያው ልክ ይጨምራል። በመሆኑም ያለው ሥራ ፈላጊዎች ቁጥር እና ያለው የሥራ እድል አሁንም በሚፈለገው ልክ ተጣጥሟል ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ባለሀብቶችን በማሳተፍ ጭምር የከተማው አቅም በሚፈቅደው ልክ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ትልልቅ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡ እንደሚታወቀው የሥራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረውና ለእድገታችንም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ የሚታመነው ኢንቨስትመንት ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ባለሀብቶች ወደ ከተማዋ እየመጡ ኢንቨስት እንዲያደርጉ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ባለሀብቶች ወደ አምቦ ከተማ መጥተው ኢንቨስት ማድረግ ይቅርና የነበሩት ራሱ ከተማውን ትተው ወደ ሌሎች አካባቢዎች የሚሄዱ ነበሩ፡፡ ከተማቸውን እንዳያለሙ ያደረጋቸው አንዱ ምክንያት የሰላም ጉዳይ ነበር፡፡

አሁን አምቦ ሰላሟን እያስጠበቀች፤ ልማቷን እያስቀጠለች ያለች ከተማ ሆናለች፤ በዚህ የተነሳ ኢንቨስተሮች ወደ ከተማዋ እየተሳቡ መጥተዋል። በርካታ ባለሀብቶች በልማት ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ በመሆኑም የሥራ እድል እየተፈጠረ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ቢያንስ ከ195 በላይ ኢንቨስተሮች መሬት ወስደው በሥራ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ አብዛኛዎቹም ከ70 በመቶ በላይ ቅድመ ዝግጅትና የግንባታ ሥራዎችን ሠርተው በአጭር ጊዜ ወደ ሙሉ ሥራቸው የሚገቡ እንደሆነ ይጠበቃል። እነዚህ ወደ ር ሲገቡ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል የሚፈጥሩ ይሆናሉ፡፡ የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ በተያዘው ዓመት ብቻ በከተማዋ 20ሺ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል፡፡ የሥራ ዕድል ፈጠራውን በተለያዩ የሥራ መስኮች ተግባራዊ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎችም በየጊዜው እየተገመገሙ ይገኛል፡፡ እቅዱ ግቡን እንዲመታም የባለሀብቱ ተሳትፎና የአመራሩ ቁርጠኝነት ወሳኝ ጉዳይ በመሆናቸው ሀብትን፣ ገንዘብን እና ጉልበትን በማቀናጀት የሥራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- የልማት መሠረቱ ሰላም ነው፤ የአምቦ ከተማ የሰላም ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት አሁን የታየው ለውጥ በሕዝቡ መስዋዕትነት የተገኘ እንደመሆኑ ለውጡን ሕዝቡ ራሱ እየጠበቀው ይገኛል፡፡ ህብረተሰቡ ለውጡን የማስጠበቅ ወይም የማስቀጠል ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበትም ያምናል። ሥርዓቱን ያመጣው ራሱ በመሆኑም ይጠብቀዋል፤ እየጠበቀውም ይገኛል፡፡ ሕዝቡ ሰላሙን የመጠበቅ ከፍተኛ ፍላጎትም አለው፡፡ ይህ የሕዝቡ የሰላም ፍላጎት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ደግሞ በእኛ በኩል መሥራት የሚጠበቅብንን እንሠራለን። ሰዎች የሚያቀርቧቸው የሰላም ጥያቄያቸው ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡ በዚሁ መሰረት ከሰፈር ጀምሮ እስከ ከተማ መዋቅር ድረስ ህብረተሰቡን እና የጸጥታ አካሉን የማቀናጀት፣ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራዎች በአመራሩ በኩል ይሠራሉ፡፡

የማህበረሰብ ፖሊስ፣ የከተማ ሚሊሻ፣ የሥርዓቱ ጋሻዎች የሚባሉት የየአካባቢው ሥርዓት አስጠባቂዎች (ሲርና ጋቻና)፣ የአምቦ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ ፌዴራል ተቋማት የተመደቡ የፌዴራል ፖሊሶች፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እንዲሁም የየአካባቢው ማህበረሰብ ተወካዮች የከተማውን ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር የየራሳቸውን ሥራ ይሠራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሁሉም የጸጥታ አካላት የተውጣጣ አደረጃጀት በመፍጠር ሁሌም በከተማውና በአካባቢው ሰላም ጉዳይ ምክክሮችና ውይይቶች ይደረጋሉ፤ በመድረኩ አሠራሮች ይገመገማሉ፤ በሰላምና ጸጥታ ጉዳይ መሠራት ስላለባቸው ነገሮች የጋራ አቅጣጫዎችም

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ‹‹አምቦ ሰላሟን እያስጠበቀች፤ ልማቷን...

ከገጽ 8 የዞረ

ይቀመጣሉ፡፡

በተለይም የሥርዓቱ ጋሻ (ሲርና ጋቸና) የሚባሉት ከማህበረሰቡ የወጡት ወጣቶች ከተለያዩ የጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢያቸውን ወይም የየቀበሌዎችን ሰላምና ጸጥታ የማስከበር ሥራ ይሠራሉ፡፡ ህብረተሰቡም ያግዛቸዋል፤ አካባቢውን እንዲጠብቅ ተልዕኮ ይሠጠዋል። ፀጉረ ልውጥ ሰዎችን ሲመለከት ዝም ብሎ ማለፍ እንደማይገባው፣ በየሰፈሩ ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች ማንነትን የማወቅ፣ በአካባቢው የሚስተዋሉ እውቅና የሌላቸው አደራጃጀቶችና እንቅስቃሴዎች ካሉ የመፈተሽ፣ አስፈላጊ ከሆነም ለሚመለከተው አካል መረጃ የመስጠት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ህብረተሰቡ የተሰጠውን ተልዕኮ በተግባር እንዲገልጽም በየጊዜው የማንቃትና የማስታወስ ሥራ ይሠራል። እንዲህ አይነት ጠንካራ አደረጃጀቶች ስለተፈጠሩ ከተማዋ ፀጥታዋ ተከብሮ ነው ያለችው፡፡ እኛም በከተማው ሰላምና ጸጥታ ጉዳይ ጠንካራ አቋም ይዘን፤ እቅድ አውጥተን ህብረተሰቡን እያንቀሳቀስንና እያቀናጀን የአምቦ ከተማ ሰላም እንዲጠበቅ፣ ልማቷም ጠዋትና ማታ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል እያደረግን እንገኛለን። በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት አምቦ ሰዎች ሰላም አጣን ብለው የሚፈናቀሉባት ሳትሆን ሰላም ፈልገው የሚመጡባት ከተማ ሆናለች፡፡ ይህ ሰላም የተገኘውም በጸጥታ ኃይሉ፣ በሥርዓቱ ጋሻዎች (ወጣቶች) በህብረተሰቡ ትብብር እና በተሠራው አደረጃጀት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን የመቻል እቅድ ይዛ በግብርናው ዘርፍ በርካታ ሥራዎችን እየሠራች ነው፤ ከዚህ ውስጥ አንዱ የከተማ ግብርና ነው፤ በአምቦ ከተማ፣ ከከተማ ግብርና እና ከሌማት ትሩፋት መርሃ-ግብሮች አንጻር ምን የተሠሩ ሥራዎች አሉ?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** ከሌማት ቱሩፋት አንጻር በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ለምሳሌ ህብረተሰቡ በግቢው ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ሁሉ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንዲተክል ማድረግ ተችሏል፤ እያንዳንዱ አባ እና እማ ወራ ከ20 እስከ 30 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች እንዲኖሩት ከተቻለም አንድ የወተት ላም እንዲኖረው በማድረግ የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪም እንደ ዩኒቨርሲቲ፣ የእምነት ተቋማትና ሌሎችም የሚሰሯቸው ሥራዎች አሉ፡፡ በወተት ላሞች እርባታ፣ በከብት ማድለብ፣ በዶሮ እርባታ ፣ በአሳማ እርባት፣ ወጣቶች በማህበር እየተደራጁ እንዲሠሩ በማድረግ እንደ ከተማ የሌማት ትሩፋት መርሃ-ግብሩ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ እየተሠራ ነው፡፡ እስከ አሁንም አበረታች ለውጥ ተመዝግቧል፡፡

ለህብረተሰቡም የሌማት ትሩፋት ምንድን ነው? ምን አይነት ጥቅም ያስገኛል? በሚለው ላይ በደንብ የማስገንዘብና የማነቃነቅ ሥራ ተሠርቷል። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ ዓመት በከተማው አቅራቢያ በሚገኝ ወንዝ ላይ ዓሳ የማርባት ሥራ ለመሥራት ከባለሀብቶች ጋር በመነጋገር ጅምር ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዓሳ የሚመረትባት ከተማ ትሆናለች፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኮሪደር ልማትን በተመለከተ በከተማዋ ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት በፊንፊኔ ከተማ የተጀመረው የኮሪደር ልማት በክልሎችም እንዲስፋፋ በስልጠና የተደገፈ የሥራ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ ይህ እንደ ሀገርም ይሁን እንደ ኦሮሚያ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት የአምቦ ከተማን የሚመጥን የኮሪደር ልማት እየተሠራ ነው፡፡ በመጀመሪያው ተግባራችን፤ ቤቶች ከመንገድ እንዲርቁ በተቀመጠው የርቀት መጠን ወይም ስታንዳርድ መሰረት ከማፍረሳችን አስቀድመን ሕዝቡ ልማቱ የእኔ ነው ብሎ አምኖ እንዲቀበል የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። የሚያምረው ከተማዬ ነው ብሎ እንዲቀበልና፤ አምኖበትም ለተግባራዊነቱ እንዲተባበር ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ የተነሳ ራሱ ህብረተሰቡ የሚፈርሱ ቤቶችን ወሰን በማካለል እና ድንበር በማስከበር ሥራዎች ላይ ተሳትፏል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ወሰኑ ተከብሮ መንገድ የማስፋፋት ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመንገዶች ዳርና ዳር የሚገኙ ግለሰቦችም በኮሪደር ልማቱ ምክንያት ሽግሽግ ማድረጋቸውን ተከትሎ የፈረሱ አጥሮችንና ቤቶችን የማስተካከል ሥራ እየሠሩ ነው፡፡ ለከተማዋ ውበትና እድገት ነዋሪው ሁሉ እየተረባረበ ነው፡፡

ከተማዋን በሚመጥን መልኩ ለዓይን ማረፊያና ለሰዎች መዝናኛ የሚሆኑ ሁለት ቦታዎችን በመምረጥም ከተማ አስተዳደሩ ራሱ ለመገንባት በያዘው አቅጣጫ መሰረት ወደ 10 ሚሊዮን ብር የሚገመት በጀት ተይዞላቸው ወደ ሥራ በመግባት ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይም ባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች በኮሪደርና በሌሎችም የልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል፡፡ አምቦ ከተማን አቋርጦ የሚያልፈውን ወንዝ የማልማት ሥራ ለመሥራትም ጥናት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከተማዋን ማራኪ ውብና ለኑሮ ተስማሚ በማድረግ የቱሪስት ማዕከል እንድትሆንና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቷ እንዲጨምር ታስቦ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- 19ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን እንደ ክልል በአምቦ ከተማ መከበሩ ለከተማዋ ምን ጥቅም አለው? አምቦ ተመራጭ የሆነችውስ በምን ምክንያት ነው? ምንስ ትርፍ አስገኘላት?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** አምቦ ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ከታገሉ አካባቢዎች አንዷ እንደሆነች ቀደም ሲል አንስተናል፡፡ በዘንድሮው ዓመት በክልል ደረጃ የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በአምቦ ከተማ እንዲከበር ተደርጓል፡፡ እውነት ለመናገር ይህ በዓል በአምቦ ከተማ መደረጉ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። ይህንን እድል የሰጠንን የክልሉን መንግሥት እናመሰግናለን። የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት የተረጋገጠው በትግል ነው፤ እውነተኛውን ፌዴራሊዝም እውን ለማድረግ የዚህ አካባቢ ሕዝቦች ከሌሎች ጋር በመሆን ትልቅ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ከተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች የመጡ እንግዶች የትግል ማዕከል በሆነችው በአምቦ ከተማ መጥተው ይህን በዓል ማክበራቸው የሚያስደስት ነው፡፡ ትርጉሙም ከፍ ያለ ነው፤ የሕዝቡን የእርስ በእርስ ግንኙነትና አንድነትም የሚያጠናክር ነው፡፡

በዓሉ በከተማዋ እንዲከበር ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የዝግጅት ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በዓሉን በማስመልከት በምእራብ ሸዋ ዞን ወልመራ ወረዳ እና አምቦ ከተማ በገጠርና በከተማ የተሠሩ የግብርና እና የልማት ሥራዎች የጨፌ ኦሮሚያ አፈጉባኤ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራማን በተገኙበት ተጎብኝተዋል፡፡ ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ የደም ልገሳ እና ለሳምንት የቆየ የባዛር እና ኤግዚቢሽን ሥነሥርዓት ተከናውኗል፡፡ በባዛሩ ላይ ከተለያዩ የክልሉ ዞኖችና ከተሞች ማለትም ከአዳማ፣ ከጉጂ፣ ከፊንፊኔ ፣ ከጂማና ከመሳሰሉት የመጡ ቢያንስ ቆጥራቸው 118 የሚደርስ ኢንተር ፕራይዞች እንዲሁም ከ100 የማያንሱ ነጋዴዎች እና ከተለያዩ ኮሌጆችና ከግል ዘርፍ የመጡ 35 የፈጠራ ሥራዎች በባዛሩ ላይ ቀርበዋል፡፡ ምርታቸውን የማስተዋወቅ፣ ግብይት የመፈጸም እና ልምድ የመለዋወጥ ሂደቶችን አከናውነዋል። በኤግዚቢሽኑ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የኦሮሞ ሕዝቦችን ባህል የሚገልጹ አልባሳትና ቁሳቁስም ለእይታም ለሽያጭም እንዲሆኑ ተደርገው ቀርበዋል፤ በዓሉ በፓናል ውይይት፣ በድጋፍ ሰልፍና በሩጫ ውድድርም የታጀበ ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ሰዓት ሀገራዊ የምክክር መድረክ ለማካሄድ አጀንዳ የማሰባሰቡ ሂደት እየተጠናቀቀ ነው፤ ሕዝቡ ከሀገራዊ ምክክሩ የሚያገኘውን ትርፍ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** እስከ አሁን ድረስ በአንዳንድ የሀገራችን ጉዳዮች በሃሳብ ሳንግባባ ማዶና ማዶ ሆነን የቆየንባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ አሁን ይህን ችግር ሊፈታ ይችላል ተብሎ የታመነበት ሀገራዊ የምክክር መድረክ ነው። እስከ አሁን ያለው ሂደት በጣም ጥሩ ነው፡፡ ህብረተሰቡም፣ በየደረጃው ያለው አመራርም፣ ይህን እድል ተጠቅሞ ለሀገሪቱም ይሁን ለሕዝቡ ጥሩ ነገር ያመጣል ብለን እናምናለን። ከዚህ አንጻር እኛም የሚጠበቅብንን እየሠራን ነው። ሀገራዊ ምክክሩ የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ እንደሀገር ያልተግባባንባቸውን ትልልቅ ጉዳዮች ተነጋግረን እልባት በመስጠት ወደ አንድ የመግባቢያ ሃሳብ ላይ እንድንደርስ ያስችለናል፡፡ የእኔ ይበልጣል፤ የእኔ ይሻላል የሚሉት የተራራቁ ሃሳቦች ወደ መሀከል እንዲመጡ በማድረግ ልዩነታችንን የምናስታርቅበት ነው፡፡ ሀገራዊ ምክክር ሃሳብና ሃሳብ ብቻ የሚንጸባረቁበት፤ ምክክርና ውይይት በማድረግ መግባባትና ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚረዳ መድረክ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እንደ ከተማ አሉን የምንላቸውን ሃሳቦች ይዘን በእያንዳንዱ ሂደት የመሳተፍ ዝግጁነት አለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከሰላምና ልማት አንጻር ለዞኑ እና ለከተማው ነዋሪዎች ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** ለከተማው ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያም ይሁን ለኦሮሞ ሕዝብ የማስተላልፈው መልዕክት፤ ይህ አሁን ያገኘነው ለውጥ ዝም ብሎ የተገኘ አይደለም። ትልቅ መስዋዕትነት የተከፈለበት ነው፡፡ ይህንን ለውጥ ለማምጣት ብዙዎች የህይወት ዋጋ ከፍለዋል፤ ደምተዋል፤ ቆስለዋል፤ ስቃይና መከራ ተቀብለዋል። ይህን በጋራ ትግል ያመጣነውን ለውጥ አንድ ሆነን ተማክረንና ተረዳድተን መጠበቅና ወደ ፊት ማሻገር ይኖርብናል፡፡ ይህ ሲሆን ብልጽግናችንን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡

ልማትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ የመጀመሪያው መሠረታዊ ነገር ሰላም ነው፡፡ የሰላም ዋጋ በምንም የሚለካ አይደለም፡፡ ሰላም ሲኖር የብልፅግና ጉዟችን እውን እንደሚሆን ተስፋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለያየ መንገድ ሰላም ለማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ወደ ሰላም መጥተው በዚህ ታሪካዊ የብልፅግና ጉዞ የድርሻቸውን እንዲወጡም እመክራለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቃለ ምልልስ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነው ውድ ጊዜዎን ስለሰጡን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ተስፋዬ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

**ልማትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ የመጀመሪያው መሠረታዊ ነገር ሰላም ነው፡፡ የሰላም ዋጋ በምንም የሚለካ አይደለም። ሰላም ሲኖር የብልፅግና ጉዟችን እውን እንደሚሆን ተስፋ ማድረግ ያስፈልጋል**

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ሴት መምህራን- ለሴት ተማሪዎች

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የአፍላነት ዕድሜ ለብዙዎች የፈተና ጊዜ እንደሆነ ይታመናል:: በርካቶች በዚህ መስመር ባለፉ ጊዜ መንገዳቸው ከብዙ አቅጣጫ ሊያደርሳቸው ይችላል:: ይህ በጎና ክፉ አጋጣሚ ታዲያ በማንነት ልክ ይመዘናል:: በአስተውሎት ፤ በጥንቃቄ የሚራመዱት ቢኖሩ ነገን በተሻለ ለማግኘት አጋጣሚው ምክንያታቸው ነው:: በዚህ አይነቱ መስመር ፈተናውን መሻገር ያቃታቸው ደግሞ ከትናንቱ ክፉ ደግ አጋጣሚ ይማሩበት ዘንድ እውነታው ያግዛቸዋል::

እነሆ! አርሲ ዞን ሂጦሳ ወረዳ ላይ ተገኝተናል:: ከኢተያ መገሪሳ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ:: ይህ ሰፊ አጸድ የተማሪዎች ዓለም ነው:: በርካቶች በደስታ ይቦርቁበታል:: ብዙዎች በአቻነት ይጣመሩበታል:: ከምንም በላይ ግን የሁሉም ዓላማና ግብ ከአንድ አይቀሬ ጥግ ያደርሳቸዋል:: ተዝቆ ከማያልቀው ትምህርትና የዕውቀት ጓዳ::

ተማሪዎቹ ዘወትር ከክፍላቸው ተገኝተው ዕወቀትን ሲቀስሙ ነገን በተሻለ ለመራመድ ነው:: ጥረት ድካማቸው ዕውን እንዲሆንም ዛሬን የበተኑት ዘር ነገ ፍሬውን ያሳፍሳቸዋል:: ለዚህ ውጤት መሳካት ደግሞ የእነሱ ጥረት ብቻውን ፋይዳ ቢስ ነው:: ለዓላማቸው ስኬት የወላጆችና መምህራን ኃላፊነት ከፍ ይላልና::

ተማሪዎች በአፍላነት ዕድሜያቸው በመልከ ብዙ ባህሪያት ያልፋሉ:: ይህ ዕድሜ በተለይ ለሴት ተማሪዎች ፈተናው የበዛ ነው:: ሴቶች በተፈጥሮ የተሰጣቸው ፀጋዎች ለውበት እንዲያደሉ ፈርጇቸዋል:: ይህ እውነት ደግሞ አፍላነት ላይ ሲሆን ትርጉሙ ይለያል::

በዚህ ዕድሜ አንዲት ሴት ልጅ በአብዛኛው ራሷን በተለየ ትኩረት የምትጠብቅበት፣ ለውበቷ የምትጨነቅበትና ከአቻዎቿ ጋር የምታዘወትርበት ነው:: ይህ ወቅት አካላዊ ለውጧ ጎልቶና ደምቆ የሚታይበት ነው:: ዕድሜዋን ተከትሎ የሚስተዋሉ ባህሪያትም ቀድሞ ያልነበሩና ያልተለመዱ አይነት ሊሆኑ ይችላሉ::

በዚህ ዕድሜ የሚስተዋሉ ለውጦች በአብዛኛው በተማሪነት ጊዜ የሚሆኑ ናቸው:: እንዲህ መሆኑ ሴት ተማሪዎችን ለበረከቱ ፈተናዎች ሊያጋልጣቸው ዕድሉ የሰፋ ነው::

መምህርት ገነት ገብሬ በኢተያ የመገሪሳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዓመታት አስተምረዋል:: መምህርቷ ውሏቸው ከጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ አስተምህሮት የተሻገረ ነው:: በየእለቱ ስለሴት ተማሪዎቻቸው ደህንነት ያስባሉ:: እሳቸው የተማሪዎቹን ችግር፣ ሀዘንና ደስታ ለማወቅ ቅርብ ናቸው:: ቅርበታቸው ደግሞ ከመምርነት አልፎ የእናትነትን ስሜት ይዋረሳል:: ሁሌም ተማሪዎቹን በፍቅር እያዩ ያዋዩዋቸዋል:: እንደ እናት ራሳቸውን ዳብሰው፣እንደ መምህርት ተቆጥተውና ገስጸው መስመር ማስያዝ ልማዳቸው ነው::

ገነት የሴት ተማሪዎች ክለብ ሰብሳቢ ናቸው:: ይህ ኃላፊነት በኢተያና አካባቢው ለሴት ተማሪዎቹ ስጋት የሚባሉ ጉዳዮችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ምክንያት ሆኗል:: ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በዙሪያ ከተማው የባጃጅ ተሽከርካሪዎች ተበራክተዋል:: የሞተር ሳይክሎች ቁጥርም ቀላል የሚባል አይደለም:: ይህ መሆኑ ለጠቀሜታው ብቻ ሚዛኑ አልደፋም:: አንዳንድ ወንዶች ሴት ተማሪዎችን በትናንሽ ስጦታዎች እየደለሉ ከስፍራው ለማራቅ ሲሞክሩ ቆይተዋል:: በጠለፋ፣ አባብሎ በመደለልና በተለያዩ ዘዴዎች ተማሪዎቹ ሰለባ የሚሆኑበት አጋጣሚም በርካታ ነበር::

ለመምህርት ገነትና መሰሎቿ በየቀኑ ይህ አይነቱ እውነታ ከዓይናቸው የራቀ አይደለም:: ሁሉም ግን እውነታውን አይተውና ሰምተው ዝም አላሉም:: ሰብሰብ ብለው በትኩረት ተወያዩ:: ውይይቱ የግላቸው ብቻ አልነበረም:: ችግሩን ለማስወገድ ከሚመለከታቸው የህግ አካላት ጋር ተጣምረው ለመፍትሔው ተጉ:: የተማሪዎችን ቤተሰቦች አወያይተው ምን ይሻላል?



ተማሪ ሀዲሳ ጀማል



ተማሪ ሴና ፈቃዱ

ማለታቸው የጥረታቸው በሳል ፍሬ ሆነ::

ዛሬ በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩ ሂደት ያለ አንዳች ስብራት ቀጥሏል:: ተማሪዎች ያለአንዳች ስጋት ወጥተው ይገባሉ:: ችግር ቢኖር ከመምህራኖቻቸው ጋር መወያየትን ለምደዋል:: የንጽህና መጠበቂያን በሚመለከት ምስጢራቸው ከሴት መምራን የተደበቀ አይደለም:: የፈለጉትን ይጠይቃሉ:: የጎደለው ይሟላላቸዋል:: በሴት ተማሪዎች ክለብ ሁሉም በግልጽ ተወያይቶ ለችግሮች መፍትሄ ይጠቁማል::

ሴት ተማሪዎች ጾታዊ ጥቃት እንዳያገኛቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ የክለቡ ኃላፊነት ነው:: ሴት ተማሪዎች በዓላማቸው ጸንተው ላሰቡት ግብ እንዲደርሱ በየጊዜው የምክር ድጋፍ አይለያቸውም:: ሁሌም ጎበዝ የሚባሉ ተማሪዎች በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ጓደኞቻቸው ዕውቀታቸውን ያጋራሉ:: በትምህርት ቤቱ ሴት ተማሪዎች በደረጃ በማለፍና ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ይታወቃሉ::

በየጊዜው ተማሪዎቹ በቤተመጽሀፍት የመጠቀም ልምዳቸውን አዳብረዋል:: በየዓመቱ የሚመዘገበው የብሔራዊ ፈተና ውጤት ከሌሎች ትምህርት ቤቶች የላቀ መሆኑ የትምህርት ቤቱን ስም በበጎ እንዲጠራ አስችሏል::

ሀዲሳ ጀማል በኢተያ የመገሪሳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነች:: ተምራ ካሰበችው ለመድረስ ትምህርት ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን ታምናለች:: ይህ እውነታ ዘወትር ከደብተሯ አይለያትም:: ጊዜዋን ለጥናት ትሳጣለች:: በሴት ተማሪዎች ክለብ መሳተፏ ደግሞ በበርካታ ጉዳዮች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራት አግዟታል::

ሀዲሳ እሷና ጓደኞቿ ሁሌም በሴት መምህራን የሚሰጣቸውን ምክር ይጠቀሙበታል:: ቅርበታቸው እንደ ተማሪ አስተማሪ ብቻ አይደለም:: ልክ እንደ እናት ቃላቸውን ያከብራሉ:: ሀሳባቸውን ይጋራሉ:: ቀደም ሲል በትምህርት ቤቱ ዙሪያ የነበሩ ስጋቶች ዛሬ ላይ የሉም:: ይህ የሆነው በሴት መምህራን ብርታት ነውና የሀዲሳ ምስጋና ከልብ ነው::

ዛሬ ላይ የሀዲሳ ህልም ሰፊ ነው:: ተምራ፣በጥረት ተጉዛ ነገን ዶክተር መሆን ትሻለች:: ለዚህ ደግሞ መነሻዋ የእክስቷ ብርታትና ጠንካራ ተሞክሮ ነው:: አክስቷ የኢተያ መገሪሳ ፍሬ ነች:: በዚህ ትምህርት ቤት ተምራ ዶክተር ለመሆን በቅታለች:: ዛሬ ይህች ሴት ለእሷ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ የአካባቢው ተማሪዎች ተምሳሌት ናት::

ሴና ፈቃዱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነች:: ሁሌም ስለማንነቷ ስትናገር ጉብዝናዋን በማስቀደም ነው:: ከሴና ይህ ጠንካራ መተማመን የተገኘው ያለምክንያት አይደለም:: ዘወትር ለትምህርቷ ትኩረት መስጠቷና ፣በጥናት መትጋቷ ልበ ሙሉ አድርጓታል:: በትምህርት ቤቱ በልዩ ክፍል ተመርጠው ከሚማሩት መሀል አንዷ የሆነችው ሴና ሁሌም ስለትምህርቷ እረፍት ይሉትን አታውቅም::

በዚህ ክፍል ሴት ተማሪዎች ከወንዶቹ የሚያደርጉት ፉክክር ጤናማ ነው:: በተለይ ሴቶቹ በውጤታቸው ፍሬያማ መሆናቸው ተተኪዎችን ለማፍራት አርአያ አድርጓቸዋል:: ሴና የሴት ተማሪዎችን ጥረትና አመርቂነት ከተለየ ዓላማና ግብ ጋር ታጣምረዋለች:: ሴቶች ነገን በብሩህ ተስፋ መቅረጻቸው አሸናፊነት ከእነሱ እንዲሆን ምክንያት መሆኑን የምትገልጸውም ራሷን ምሳሌ በማድረግ ነው::

ረሂማ መሀመድ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነች:: የትምህርት ጥቅምን ካወቀች ወዲህ ዶክተር የመሆን ፍላጎቷ ጨምሯል:: ለዚህ የምትሰጠው በቂ ምክንያት ባይኖርም ሰውን መርዳት በራሱ እንደሚያስደስታት ትናገራለች:: ረሂማ ከወንድ መምህራን ይበልጥ ለሴቶቹ ቅርበት አላት:: በተለየ በፍቅር ስለሚቀርቧትም የውስጧን ፍላጎት አትሸሽጋቸውም:: ዛሬን በጥንካሬ ተምራ ለነገ ዓላማዋ እንድትደርስ ለምክርና ተግሳጽ ውስጧ ዝግጁ ነው::

ዲና አላማን ደግሞ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ናት:: በመገሪሳ ኢተያ ትምህርት ቤት ቆይታዋ የቀሰመችው የቀለም ዕውቀትን ብቻ አይደለም:: በቆየችባቸው ስምንት ዓመታት ከዕድሜዋ ብዙ ተምራለች:: ዲና ቀደም ሲል በአካባቢው ስጋት ሆኖ የቆየው የሴቶች ጥቃት አሁን ላይ እንደሌለ ትናገራለች::

ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ሴት መምህራን ከሴት ተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ጤናማ ግንኙነት ነው:: በትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎች ክለብ መቋቋሙና ጠንካራ ተሳትፎ መኖሩም ለብዙ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል:: ዛሬ ሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ለመጠየቅ አያፍሩም:: ወላጆቻቸውም ስለሴት ልጆቻቸው ያላቸው አመለካከት ተቀይሯል:: ከወንዶች እኩል ተምረው እንዲገቡ ዕድሉን አይነፍጉም::

ዲና የነገ ህልሟ በምህንድስና ሙያ ሀገርና ወገኗን ማገልገል ነው:: ይህን ለማሰቧ የምታስቀምጠው ምክንያት ደግሞ በማንነቷ የምታኖረውን ደማቅ አሻራ ነው:: እሷ ከወንዶች ባላነሰ ሙያዋን ማሳየት፣ ስራዋን ማስመስከር ትሻለች:: በራሷ የአዕምሮ ዕውቀትም ትምህርት ቤትና ሆስፒታል የመገንባት ህልም አላት:: ይህን ለመከወን ጠንክሮ መማር ወሳኝ እንደሆነ አሳምራ ታውቃለች::

ለዚህ ፍላጎቷ ደግሞ የመሸጋገሪያ ድልድይ የሚሆናት ወደፊት ልትማረው ያሰበችው የምህንድስና ሙያ ነው:: ዲና ይህ ዕውን ይሆን ዘንድ የመሰረት ድንጋይ የምታኖረው ከዛሬ በመነሳት እንደሆነ በእርግጠኝነት ትናገራለች:: ብርቱዋ ተማሪ ትምህርቷን በወጉ አጠናቃ ላሰበችው ዓላማ ለመድረስም ትጋቷን ከወዲሁ በተግባር እያሳየች ነው::

ሁሌም ቢሆን በሴት መምህራን ድጋፍና ምክር ለነገ ህይወቷ በጎነትን እንዳተረፈች ትናገራለች:: የሰባተኛ ክፍል ተማሪዋ መኪያ ጣሂር:: እሷን ጨምሮ ሌሎች ሴት ተማሪዎች በወንዶች በቀላሉ እንደሚታለሉ አትደብቅም:: መኪያ ወንዶች የምትላቸው አብረዋት የሚማሩትን አይደለም:: ስለእነሱ ያላት ስሜት ፍጹም መልካምና ጤናማ ነው:: አብዛኞቹን የወንድም ያህል ትቀርባቸዋለች:: ከልጅነታቸው ጀምሮ በአንድ የዕውቀት ገበታ ላይ ቆይተዋል:: ስለእነሱ ያላት ግምትና አመላካከትም ተቀይሮ አያውቅም::

መኪያ ለእሷና ለሴት ጓደኞቿ ስጋት ናቸው የምትለው በትምህርት ቤቱ ዙሪያ የሚያንዣብቡት አንዳንድ ወንዶችን ነው:: እነሱ ማለት ለትምህርት ቤቱ ሴት ተማሪዎች እንደ ጭቃ እሾህ ይቆጠራሉ:: አድብተውና ድምጽ አጥፍተው ለማጥቃት ወደኋላ አይሉምና::

መኪያ እንዲህ አይነቶቹን ወንዶች «የሰውነት ክብር ያልገባቸው»ስትል ትገልጻቸዋለች:: መንገድ ላይ ተቀምጠው ሴትን ልጅ ሲያስቸግሩና ሲጎነትሉ ሀፍረትን ይሉትን አያውቁም:: እንዲህ ማድረግ ደግሞ መብትን ከመንጠቅና ከመጋፋት በላይ ነው::

ምን አልባት አንዳንድ የእሷ እኩዮች አንደንዴ በእነሱ ተታለው ከእጃቸው ሊወድቁ ይችላሉ:: ማወቅ ያለባቸው ግን የዛሬን ሳይሆን የነገውን ህይወት ብቻ መሆን እንደሚገባ ትመክራለች:: በእሷ ግምት እነዚህ ወንዶች ሁሌም ለመዋሸት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም:: በእንዲህ አይነቶቹ ተታለው አጉል ከሆኑ ሴቶች ተሞክሮ ደግሞ ብዙ መማር ይቻላል::

እኔ የመኪያ ሀሳብና ንግግር ከዕድሜዋ በላይ ቢመስለኝ በእጅጉ መገረም ይዣለሁ:: ግርምታዬን በውሰጤ ማስቀረት አልፈለኩምና ቀሪ ሀሳቧን ለማድመጥ ጊዜ ሰጠኋት:: መኪያ በዚህ ጉዳይ ላይ አምርራ የምትናገረው ያለ ምክንያት አይደለም:: ይህ ርዕስ በተነሳ ቁጥር የቅርብ ባልንጀራዋን ክፉ አጋጣሚ ታወሳለች:: ይህች ጓደኛዋ የልቤ የምትላት ወዳጇ ናት:: ምስጢረኞች ናቸውና የውስጣቸውን አይደባበቁም:: በየዕለቱ ያጋጠማቸውን ያወጋሉ፤ ይመካከራሉ::

ጓደኛዋ በአንድ ወቅት ካልተገቡ ጓደኞች ጋር ውላ ካላሰበችው ወጥመድ ወደቀች:: ይህን ያስተዋሉ ወላጆች ሁኔታው ቢያሳስባቸው ሊመክሯት፣ ሊገስጿት ሞከሩ:: «ጆሮ ዳባ ልበስ» ያለችው ልጅ ግን ልትሰማቸው አልወደደችም:: ምክራቸውን ንቃ በመንገዷ ቀጠለች::

የመኪያ ጓደኛ ውላ አድራ ለጉዳት መጋለጧ አልቀረም:: ይህ ክፉ አጋጣሚ ደግሞ ለእሷና ለሌሎች ህይወት ማሳያ ሆኖ ዛሬ ድረስ እንደምሳሌ ታነሳዋለች:: ጓደኛዋ አሁን ላይ በቤተሰብ፣ በጓደኞቿ እገዛና ምክር ወደ ትምህርቷ ተመልሳለች:: ይሁን እንጂ የረገጠችው አጉል መንገድ ለዕድሜዋ ስብራት ሆኖ በፈተናዎች መሰናክል ልታልፍ ግድ ብሏል::

እንደ መኪያ ያሉ ብርቱ ተማሪዎች ስለ ነገ ህይወታቸው የሚያስቡት አስቀድመው ነው:: ወላጆቻቸው ወደ ትምህርት ሲልኳቸው ጠቀሜታው ለእራሳቸው መሆኑን አሳምረው ያውቁታልና ምክርና ተግሳጽ አያሻቸውም::

አንዳንዴ ደግሞ የልጅነት ዕድሜና የአቻ ግፊት የፈተናቸው ተማሪዎች በአጉል መስመር ላይ ሊገኙ ይችላሉ:: እነዚህ ተማሪዎች በተለይ ሴቶች ከሆኑ ከወንዶቹ ይልቅ ለችግር የተጋለጡ ይሆናሉ:: እንዲህ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተማሪዎቹን እንደ ልጆቻቸው መክረውና ገስጸው ለመመለስ የሴት መምህራን አበርክቶ ይጎላል::

የሴት መምህራን ዓላማ ማስተማር ብቻ አይደለም:: ተማሪዎቻቸውን እንደልጆቻቸው በማየት ከመልካም ጎዳና ያደርሳሉ:: ችግር ሲደርስ ብቻ ሳይሆን አስቀድመው በመምከርና በማቅረብ ቤተሰባዊ ፍቅርን ለመለገስ የራቁ አይደሉም:: ይህ እውነት በተለይ ሴት ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸውን በበጎ አቅጣጫ እንዲመሩና በስርዓተ ጾታ ታንጸው እንዲዘልቁ ለማድረግ ብርታት ይሆናቸዋል::

በአርሲ ሂጦሳ ወረዳ የመገሪሳ ኢተያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሞክሮና አርአያነት ለሌሎች ጭምር የሚሻገር ነው:: ሴት መምህራን ለሴት ተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ትኩረትም ወደፊት ሀገር ተረካቢ ለሚሆነው ትውልድ መሰረት ይሆናል:: ሁሌም «ሴትን ልጅ ማስተማር ሀገርን ማስተማር ነው» እንዲሉ የትምህርት ቤቱ መልካም ተግባራት ስለ ነገ መሰረት ለመጣል ጠንካራ ጡቦችን አኑሯልና::

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# አልማዝ የሚለበስበት የፋሽን ትዕይንት

ቤዛ እሸቱ

የፋሽን ትዕይንቶች (ሾዎች) ባደጉት ሀገራት የተዘጋጁ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ከማሳየት አልፈው ብዙ ርቀው ሄደዋል:: የፋሽኑና የመዝናኛው ዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪዎች በሚዘጋጁ የፋሽን ትዕይንቶች ላይ ለመታደም አሕጉር አቋርጠው ሲጓዙ ማየት ተለምዷል:: በተለይ የፈረንሳይዋ ፓሪስ፣ የጣልያኗ ሚላን የአሜሪካኗ ኒውዮርክና የእንግሊዟ ለንደን ከተሞች የሚዘጋጁትና በከተሞቹ በተሰየሙት የፋሽን ሳምንታት መሳተፍ ለፋሽኑ ዘርፍ ባለሙያዎች ትልቅ ትርጉም አለው:: ከተሞቹ ያን ሰሞን በጎብኚ ይጨናነቃሉ:: የፋሽን ኢንዱስትሪው ገበያ ይደራለታል::

በፋሽን ሳምንታቱ ማን ሥራውን አቀረበ?፤ የትኛው ታዳሚ ተገኘ?፤ የትኛው መገናኛ ብዙኃን ምን ዘገበ?፤ የዓለማችን ተፅዕኖ ፈጣሪዎች የትኛውን ልብስና ጫማ ተጫሙ?፤... ብቻ ብዙ ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ይነሳሉ::

ታዲያ በየመድረኩ ሥራቸውን የሚያቀርቡ ዲዛይነሮች፣ በመድረኩ ሽር ብትን የሚሉ ሞዴሎች፤ የተመረቱትን ምርቶች ገዝተው ለቀጣይ የሚሸጡ ነጋዴዎች፤ የመድረክ ገጽ ግንባታ ባለሙያዎች፤ በመድረኩ ሥራቸውን የሚያቀርቡ የሙዚቃ ባለሙያዎች፤ መድረክ መሪዎች፤ የአልባሳትና የጌጣጌጥ አምራች ፋብሪካዎች በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ከሚሆኑት ባለፈ በፋሽን ሾው የቀጥታ ተጠቃሚ ከሆኑት ጥቂቶቹ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ የተሠራውን አይተው፣ በመስኩ ለመሠማራት የሚነሳሱ በርካቶች ሲሆኑ ለእንግዶቹ አገልግሎት በመስጠት (የሆስፒታሊቲ ዘርፍ) በርካቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ::

በሀገራችንም የፋሽን ትዕይንቶች ሲዘጋጁ ማየት የተለመደ ቢሆንም ከተወሰኑት በስተቀር ቋሚ ጊዜ የላቸውም:: ዲዛይነሮቹ ሲሞላላቸው ይዘጋጃል፤ ሳይሆን ሲቀር ይቀራል:: በሀገራችን በዘርፉ ካለው የተለየ አልባሳት፤



**ታኅሣሥ 4 ቀን 2017 ዓ.ም ‹‹አዲስ ፋሽን ዊክ›› በሚል ስያሜ ተዘጋጅቷል**

የጥሬ እቃ ሀብት፤ የባሕል አልባሳት ስብጥር አንጻር መጠቀም ያለብንን ሳንጠቀም ቆይተናል:: ይህን ክፍተት ከመሙላት አንጻር የበኩሉን ድርሻ ሊያበረክት የሚችል የፋሽን ሳምንት ታኅሣሥ 4 ቀን 2017 ዓ.ም ‹‹አዲስ ፋሽን ዊክ›› በሚል ስያሜ ተዘጋጅቷል:: የፋሽን ትዕይንቱ በሜሊስ ፋሽንና በብሊንግ ኤቨንትና ኢንተርቴመንት የተዘጋጀ ነው::

ሜሊስ ፋሽን የዓለም አቀፍ ልምድ ባላት ዲዛይነርና ሞዴል ሜላት ሚካኤል እ.አ.አ በ2020 የተመሠረተ የፋሽን ድርጅት ነው:: ድርጅቱ በቻይና በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ ሱቆች ጋር በአጋርነት እንደሚሠራ የፋሽን ሳምንቱን መዘጋጀት አስመልክቶ በተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ ተገልጿል:: በዘርፉ ከአስር ዓመት በላይ ልምድ እንዳላት የተገለጸ ሲሆን በመድረኩ ከ40 በላይ የሚሆኑ በዲዛይነሯ የተሠሩ ልብሶች ይቀርባሉ::

የፋሽን ሳምንቱን በአጋርነት ያዘጋጀው የብሊንግ ኤቨንትና ኢንተርቴመንት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ብሊንግ ኀይትያም በመድረኩ ፋሽንን ከቴክኖሎጂ ጋር አጣምረው ለማቅረብ መነሳታቸውን ይገልጻል::

የፋሽን ዲዛይነሯ በተለያዩ ሀገራት የቀሰመችውን ልምድና ተሞክሮ ይዛ ወደ ሀገሯ መግባቷንና በሥራዋ የሀገሯን ባሕል ከዘመናዊ ጋር በማዋሓድ ለዓለም ለማስተዋወቅ ስትነሳ፤ በሀሳቡ በመስማማታቸው አብረው እየሠሩ መሆኑን አስረድቷል:: መድረኩ ፋሽን በኢትዮጵያ እንደሚጠቅም የምናሳይበት ኢትዮጵያን እንዴት እናስተዋውቅ ብለን የተለየ ነገር ይዘን የመጣንበት ነው ብሏል ዳይሬክተሩ::

እንደ ብሊንግ ማብራሪያ፤ የፋሽን ትርዒቱ ከመድረክ ግንባታ፣ ከድምፅ፣ ከላይት አጠቃቀም ጀምሮ እስከዛሬ በሀገራችን ከተለመዱ የፋሽን ትርኢቶች በተለየ መልኩ ለመምጣት የተዘጋጁበት ነው:: ዝግጅቱ ላይ ለሚታደሙ ሰዎች የተሰራጨው የመጥሪያ ካርድ በተለየ መንገድ ዲጂታል ካርድ ተጠቅመዋል:: ተጋባዦች የጥሪ ካርዱን ሲከፍቱ ከሚነበብ ጽሑፍ ይልቅ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለዝግጅቱ እንዲታደሙ ጥሪ የምታስተላልፍ ሞዴል የቪድዮ መልዕክት ይጠብቃቸዋል:: የዘመኑ ሴቶች ውበት መጠበቂያ የሆነው ጥፍር የፋሽን ሾው አካል ሆኗል:: ጥፍሩ ‹‹በቺፕ›› መልክ የተዘጋጀ ሲሆን ጥፍሩን የሚጠቀሙ ሴቶች የግላቸውን መረጃ ለአብነት የስልክ ቁጥር የማኅበራዊ ድረ ገጾች ከስልካቸው ጋር በመገናኘት በቀላሉ መረጃዎችን ይይዛል:: የጥፍሩ ‹‹ቺፕ›› በመድረኩ ለታዳሚዎች ይሰጣል::

እንደ ዲይዛነሯ ማብራሪያ፤ በአዲስ ፋሽን ሳምንት ላይ ከ40 በላይ በዲዛይነሯ የተዘጋጁ ልብሶች ይቀርባሉ:: በመድረኩ ከ15 እስከ 20 የሚደርሱ ተሰጥዖ እያላቸው ዕድሉን ያላገኙ ሞዴሎች በዲዛይነሯ የተዘጋጁ ልብሶችን ለብሰው በመድረኩ ይዋባሉ:: ፋሽን ትዕይንቱ ቀጣይነት እንደሚኖረው የተገለጸ ሲሆን፤ በመድረኩ የባሕል መሣሪያ በተለይ በመሰንቆና በክራር የታጀበ ነው:: የባሕል አልባሳታችን የክት ልብስ ከመሆናቸው በተጨማሪ በአዘቦት ጥቅም ላይ ለማዋል ምቹ ሆነው መዘጋጀታቸው ተነግሯል::

የፋሽን ዲዛይነሯ ለኢትዮጵያ መድረክ አዲስ ስለሆነች የአሁኑ ሥራዎቿን ለማስተዋወቂያ በአንድ ቀን ቢጠናቀቅም፤ በቀጣይ በየስድስት ወሩ የሌሎች ፋሽን ዲዛይነሮች ሥራ በመቀላቀል ይዘጋጃል:: ዲዛይነር ሜላት በተለይ ተሰጥዖ እያላቸው ዕድል ያላገኙ ወጣት ዲዛይነሮችን በማካተት ለዓለም ገበያ ሥራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት እድል ለማመቻቸት እንደሚሠሩ ተናግራለች:: ያኔ የበርካታ ዲዛይነሮች ሥራ ሲካተት ልክ እንደስሙ የፋሽን ሳምንት ይሆናል::

በሀገራችን ነገሥታት ከወርቅ የተሠሩ ዘውድ፣ ጫማዎች እንደነበሯቸው በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሙዚየሞች አስረጂ ናቸው:: በቀደመው ጊዜ ኑሮ የሞላላቸው ወርቅን የማጌጫ አይነት ከማድረግም ባለፈ የቀሚሳቸው ማስጌጫ ነበር ሲባል በታሪክ ሰምተናል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን ለመመለስ በምትሠራቸው ልብሶች ላይ በትእዛዝ በወርቅና በብር የምታስውብ ዲዛይነር ተመልክተናል:: ታኅሣሥ አራት በሚካሄደው አዲስ ፋሽን ዊክ ላይ ደግሞ አንድ ምዕራፍ ተሻግሮ ሁለት በአልማዝ የተሠሩ መኖራቸው ተጠቁሟል::

የፋሽን ሳምንቱ ታኅሣሥ አራት ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 11፡00 ላይ በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ይጀመራል:: በዕለቱ ወጣቷ ድምፃዊ ዊሃ የሙዚቃ ሥራዋን ታቀርባለች:: ድምፃዊቷ በዲዛይነሯ የተዘጋጁትን ልብሶች ለብሳ የሙዚቃ ሥራዋን የምታቀርብና ልብሶቹን የምታስተዋውቅ ይሆናል:: ዝግጅቱ ያለምንም ክፍያ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በመጥሪያ ካርድ የሚታደሙበት መሆኑ ተነግሯል::

# ትዝብት/ ማረፊያ

# ደንበኛ ሞኝ ነው?

ሂሳሪያ ተስፋዬ

### ንጉሥ ነበር ደንበኛ፣ ድሮ ነው እሱ።

ድሮ ስል መች ነው ግን? የጊዜው አሯሯጥ የ'ድሮ'ን ርቀት መለኪያ የሆነውን መስፈርት ያጠፋው ይመስላል። እርግጥ ነው፣ ድሮ ሲባል የቀደሙ ወላጆቻችንን ዘመን እየጠቀስን ይመስላል። አሁን ላይ ግን ድሮ የሚለው 'ነገር' በክፍለ ዘመን አቆጣጠር መሆኑ ከቀረ ሰነባብቷል።

ለምሳሌ "በአምስት ብር ሂሳብ ተሳፋሪ ጭኖ ከተጠቀሰ አንድ ስፍራ የሚያደርስ ታክሲ ነበር።" ሲባል፥ ይህ ጉዳይ የዛሬ ሀምሳና አርባ ዓመት የሆነ የሚመስለው ተሳስቷል። ይህ የዛሬ አምስትና ስድስት ወር አካባቢ ታሪክ ነው። እንጀራ 15 ብር ይሸጥ ነበር ሲባልም እንደዛው፣ የጥንት ታሪክ ሊመስል ተቃርቧል።

በድምሩ፥ ይህን ሁሉ መዘብዘቤ፣ ድሮ የሚለው 'ጽንሰ ሐሳብ' ትላንት ወደሚለው የጊዜ መጠቆሚያ እየቀረበ ነው ለማለት ነው። ድሮ ታድያ ምን ነበር፥ ደንበኛ ንጉሥ ነበር።

ደንበኛ ንጉሥ ነበር፥ ቃሉ ይደመጣል፣ ቅሬታው ይስተናገዳል፣ መከፋቱ ጆሮ ይሰጠዋል፣ ቢሳሳትም እንኳ አይሳሳትም ትክክል ነው፣ ሳያጠፋ ይቅርታ ይጠየቃል፣ ሳይጠይቅ መልስ ይሰጠዋል፣ ምርጥ እቃ ሁሉ ይቀመጥለታል፣ ልዩ ቅናሽ ይደረግለታል ወዘተረፈ።

አሁን አንድ ሰው "ደንበኛዬ ጋር ሄጄ አንድ እቃ ልገዛ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው? አንደኛ በዋጋ አንጻር ቅናሽ እንደሚያገኝ ይተማመናል፣ ሁለተኛ የሚያገኘው ምርት ጥራት ያለው እንደሚሆንና የማይሆን እቃ ነጋዴው እንደማያቀርብለት እርግጠኛ ነው፣ ሦስተኛ አስር ቦታ እየገባ 'ይሄ ስንት ነው፣ ዋጋ ቀንሱልኝ ተወደደ፣ ብዛቱ ይጨመርልኝ አነሰ፣ መርቅ እመርቅሃለሁ' እየተባባለ ከመድከም ይተርፋል።

ይህ ሁሉ ነገር ታዲያ አሁንስ ከድሮው በምን መልኩ ተቀየረ? በብዙ መልኩ ተቀይሯል። የደንበኝነት ጥቅማ ጥቅሞች ብዬ የማስባቸው ጉዳዮች በሙሉ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ፣ ነፋስንም እንደመከተል እንደሆኑ እንዲሰማኝ ያደረገ አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ። ጉድ!

ገጠመኙን ልንገራችሁ።

ከቤተሰብ ጋር ሆነን ሞባይል ለመግዛት ረዘም ላለ ጊዜ ደንበኞችን ወደምንላት ባለሱቅ አቀናን። ለሞባይል መግዣ የያዝነው ገንዘብ በዕቁብም፣ በብድርም፣ በውለታም የተገኘ ነውና ግዢውን በጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል በርከት ብለን ነበር የሄድነው።

እኔ ነበርኩ፥ ከደንበኛዬ ውጭ ሌላ የትም አንሄድም ብዬ አብረውኝ ስልክ ለመግዛት የተሰማሩ አጃቢዎቼን ያሳመንኩት። "አምናታለሁ፣ በዛ ላይ ሱቋ በብዙ አማራጮች የተሞላ ነው። በዛ ላይ አውቃታለሁ፣ ታውቀኛለች፥ ልትሸውደኝ አትሞክርም።" ብዬ ኡ ኡ አልኩኝ። ከመካከላችን አንዱ ወንድሜ ብቻ ነጠል ብሎ፥ "እናንተ እዚህ እስኪታዩ ድረስ እኔ ዞር ዞር ብዬ ገበያውን ልመልከት፣ ዋጋውንም ልይ" ብሎን ሄደ።

ደንበኛዬ ጋር ገባን፥ እንደተለመደው በፈገግታ አስተናገደችን። ከዚህ ቀደም ስለገዛነው ምርት፣ ስለመጥፋታችን፣ ስለምርቶች መወደድ፣ ባለፈው አብረን ሞባይል ልናጋዛው መጥተን ስለነበረው ጓደኛችን... ብዙ አወጋን። ከዛ ልንገዛ የመጣነውን እቃ ስንነግራት ዋጋ ነገረችን። ትንሽ ወደድ ማለቱን፣ የኑሮውን መቀያየር፣ እነሱ ራሱ ዋጋውን መጥራት እንዴት እንደሚከብዳቸው አያይዘንም ለልጆች ስልክ መስጠት እንደማይገባ፣ ስልክን ከሌባ፣ ከውሃና እና መሬት ላይ ከመውደቅ ምን ያህል መጠበቅ እንዳለብን መከረችን፣ ብዙ ተወያየን።

ሞባይሉ ተመረጠ፣ ዋጋ ስትነግረንም "ትንሽ ቀንሽ እንጂ" ስትል አብራኝ ገበያ የወጣች ጓደኛዬ፣ እኔ በአንጻሩ "የለም! ለእኔ ሁሌ ነው የምትቀንስልኝ፣ አትጫኗት" ብዬ በምልክትም፣ በሹክሹታም ተከራከርኩ።

ልንገዛ ተስማምተን የመጨረሻው ውሳኔ ላይ ልንደርስ ስንል፥ ሌላውን ገበያ ሲያይ የቆየው ወንድሜ ከተፍ አለ። ልንገዛ ያለውን ሞባይልና ዋጋውን ስንነግረው ፊቱ ተቀየረ። "ሻይም ጠጥተን፣ ገንዘቡንም በጥሬ አውጥተን ተመልሰን እንመጣለን፣ ሞባይል ባንኪንግ አንጠቀምም. . ." የመሳሰለውን ቀበጣጥሮ እንድንወጣ አደረገን።

አኳኋናችን መኪና ሊገዛ አማራጩን በደንብ ማየት እንደፈለገ ባለሀብት እንጂ መካከለኛ ደሞዝ እንዳለውና ሙሉ የአንድ ወር ደሞዙን ወጪ አድርጎ ሞባይል ለመግዛት እንደተሰማራ ሰው አይመስልም። ግርርርርር ብለን ከሱቁ ወጣን።

ግራ ገባኝ።

ይሄኔ ነው "ሆ ሆይ! ደንበኛ ንጉሥ ነው ያለው ማን ነው? ደንበኛ ሞኝ ሆኗል!" ያለን።

"እንዴት?" ጠያቂ እኔ ነኝ።

"እንዴ! ደንበኛኮ አሁን ሞኝ ተብሏል። ደንበኛ ስላችሁ ያው መደበኛ ተጠቃሚ የሚባለው ማለቴ ነው" አለ፥ ሊያስረዳ።

"እኮ እንዴት?" አልኩኝ፥ መቼም ጊዜ የማያመጣው የለ!

"ደንበኛ ስለሆንሽ ሌላ ቦታ እንደማትጠይቂ ያውቃሉ፣ ዋጋ እንደማታወዳድሪ፣ በጥራቱ ጥርጥር እንደሌለሽም እንደዛው። የጠሩልሽን በጠሩልሽ ዋጋ እንደምትገዢ አይጠራጠሩም። ስለዚህ፥ እንደውም ሞቅ ያለ ዋጋ የሚጭኑት ደንበኞቻቸው ላይ ሆኗል። አዲስ ደንበኛ ግን ተከራክሮ፣ ተጨቃጭቆ፣ ገበያ አነጻጽሮ ነው የሚገዛው።" አለ፥ ያለማንገራገር የተሻለ ዋጋ አለበት ወዳለው ሱቅ እየመራን።

"የምርህን ነው?"

"እውነቴን ነው። አንዷ ደንበኛዬ ናት አምልጧት ከዚህ በፊት የነገረችኝ። ተጨማሪ ትርፍ የሚያገኙት እንደውም ከደንበኞቻቸው ነው።"

ማመን ከበደኝ። ደንበኛቸው ነኝ ብዬ ያሰብኳቸውን ባለሱቆች ሁሉ አሰብኩ። ግፍ ሲፈጸምብኝ የኖረ መሰለኝ።

"የምርህን ነው?" ደግሜ ጥያቄ አነሳሁ። "እና አንድ ቋሚ ደንበኛ መያዝ ነዋ ሞኝነት?" አልኩኝ።

"በይ ደግሞ ይህንንም ጻፊውና ያነበበው ሁሉ መጠራጠር ይጀምር! ሁሉንም ማለት አይደለም..." አለኝ ሳቅ እያለ። እኔ ግን ነገሩን ማሰላሰል ማቆም አልተቻለኝም። ደንበኛ ሞኝ ነው? እንጃ! ብቻ ደንበኛዬ ያልኳት ባለሱቅ ያሳየችኝን ሞባይል ራሱን፥ እርሷ ከጠራችው ዋጋ በቀነሰ መጠን ከሌላ ሱቅ ገዝተን ወጣን። ይኸው ለእናንተም ነገርኳችሁ!

# ዓለም አቀፍ



## ዶናልድ ትራምፕ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪን ከሩሲያ ጋር ለመደራደር ዝግጁ ናቸው አሉ

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ከሩሲያ ጋር ለመደራደር ዝግጁ መሆናቸውን ዶናልድ ትራምፕ ከውይይቱ በኋላ ትሩዝ ሶሻል በተሰኘው የማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል። "በዩክሬን ጦርነት ብዙ ሰው ሞቷል፣ ብዙ ቤተሰብ ፈርሷል እስካሁን የሆነው በቂ ነው፣ ጦርነቱ ሊቆም ይገባል" ሲሉም ዶናልድ ትራምፕ ጽፈዋል።

በአሜሪካ ከአንድ ወር በፊት በተካሄደ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ በፓሪስ ታይተዋል። ተመራጩ ፕሬዚዳንት ወደ ፓሪስ የመጡት ከሦስት ዓመት በፊት የእሳት አደጋ የደረሰበት ዝነኛው ሮተርዳም ቤተ ክርስቲያን ታድሶ ለጎብኚዎች ክፍት ለማድረግ በተዘጋጀ ፕሮግራም ላይ ለመታደም ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም ዶናልድ ትራምፕ፣ የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን እና የዩክሬኑ አቻቸው ቮሎድሚር ዘለንስኪ የሦስትዮሽ ውይይት አካሂደዋል።

"ሩሲያ እና ዩክሬን የሠላም ስምምነት በቅርቡ እንደሚፈራረሙ ይጠበቃል፣ ይህ እብደት መቆም አለበት" ሲሉም ትራምፕ አክለዋል። ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ በበኩላቸው ዶናልድ ትራምፕ ስለ ሠላም የሚያደርጉትን ጥረት አድንቀው ሠላም ለዩክሬን እና ለሩሲያ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ይህ የሦስትዮሽ ውይይት በተጠናቀቀ በሰዓታት ውስጥ ተሰናባቹ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ለዩክሬን አንድ ቢሊዮን ዶላር ገደማ የጦር መሣሪያ እርዳታ የመስጠት እቅድ እንዳላቸው ይፋ አድርገዋል።

## መነኩሴዋ የወንጀለኞች ቡድን ከሆነ ማፊያ ጋር አብረው ይሠራሉ በሚል ተጠርጥረው ታሰሩ

የጣሊያን ፖሊስ በወንጀለኛ ቡድን ላይ ከሚያደርገው ምርመራ ጋር በተያያዘ 24 ሰዎችን በቁጥጥር ሥር ያዋለ ሲሆን፣ ከታሰሩት መካከል አንዲት መነኩሴ እንደሚገኙበት ተገለጸ። በሰሜን ጣሊያን ከሚደረገው የወንጀለኛ ቡድን (ማፊያ) ምርመራ ጋር በተያያዘ የታሰሩት መነኩሴ አና ዶኔሊ ይባላሉ።

ንዴራንጌህታ የተባለው የማፊያ ቡድን አባላት ሲታሰሩ ለቡድኑ አባላት መልዕክት የሚያስተላልፉት እኚህ መነኩሴ እንደሆኑ ፖሊስ ያምናል። ከዚሁ ዘመቻ ጋር በተያያዘ ፖሊስ ሁለት ፖለቲከኞችንም አስሯል። በተጨማሪም በሎምባርዲ፣ በቬኒቶ እና ካላብሪያ ከተሞች ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዩሮ በላይ የሚያወጣ ሃብት ንብረት በቁጥጥር ሥር አውሏል።

ማፊያ የተባለው የወንጀለኛ ቡድኑ በአውሮፓ አደገኛ ከሚባሉ ቡድኖች አንደኛው ሲሆን፣ ፖሊስ ለአራት ዓመታት ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። ምርመራውን ያካሄዱት የፖሊስ ባልደረቦች ባወጡት መግለጫ እንዳሉት፣ መነኩሴዋ እስር ቤት በነፃነት የመግባት እና የመውጣት መብታቸውን ተጠቅመው በወንጀለኛ ቡድኑ አባላት መካከል መረጃ ሲያቀባብሉ ነበር።


"ማንም እሷን አይጠረጥርም። በሃይማኖት ምክንያት ወደ እስር ቤቱ በነፃነት መግባት እና መውጣት ትችል ነበር" ሲል መርማሪ ቡድኑ አስታውቋል። ከምርመራው በኋላ የታሰሩ ፖለቲከኞችን ማንነት እንዲሁም ከወንጀል ቡድኑ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል የተመረመሩትን ማንነት ይፋ አላደረገም። ፖሊስ አሁንም በሰሜን ጣሊያን ፍተሻ እያደረገ ይገኛል።




በአነፍናፊ ውሾች በመታገዝ መሣሪያ፣ አደንዛዥ ዕፅ እና ገንዘብ እየተፈለገ ነው። የወንጀል ቡድኑ ቁርጥራጭ ብረት በመሸጥ ስም ሕገ ወጥ ገንዘብን ወደ ሕጋዊ መስመር ያስገባ እንደነበር ፖሊስ አስታውቋል። የወንጀል ቡድኑ መነሻ ካላብሪያ ከተማ ስትሆን ከአውሮፓ ባሻገር በዓለም አደገኛ ከሚባሉ ቡድኖች መካከል አንደኛው ነው።

ያለፈው የአውሮፓውያኑ ዓመት ላይ በጣሊያን ታሪክ ትልቁ በተባለ በማፊያ የወንጀለኛ ቡድን አባላት ላይ በተካሄደ የፍርድ ሂደት ላይ 200 ሰዎች ከሁለት ሺህ 200 ዓመታት በላይ እስር ተፈርዶባቸዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት



# የኢትዮጵያ ዋንጫ ሁለተኛ ዙር ጨዋታዎች በቀጣይ ወር ይካሄዳሉ

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ዋንጫ ለሦስት ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ከተቋረጠ በኋላ በ2016 ዓ.ም ወደ ውድድር እንደተመለሰ ይታወሳል። ይህ አንጋፋ ውድድር ዘንድሮም ቀጥሎ እየተካሄደ ሁለተኛ ዙር ላይ ደርሷል። የሁለተኛ ዙር ጥሎ ማለፍ ጨዋታዎችም በቀጣዩ ወር መገባደጃ በተመረጡት ሜዳዎች የሚካሄዱ ይሆናል።

ከኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ቀጥሎ በርካታ ክለቦችን የሚያሳትፈውና ትልቅ የውድድር መድረክ የሆነው የኢትዮጵያ ዋንጫ የሁለተኛ ዙር ጥሎ ማለፍ ጨዋታዎቹን በመጪው ታኅሣሥ ወር እንደሚደረጉም ታውቋል።

በመጀመሪያው ዙር የማጣሪያ ውድድር የአንደኛ ሊግና የከፍተኛ ሊግ ክለቦችን በማሳተፍ ወደ ሁለተኛ ዙር ያለፉ ክለቦች የተለዩ ሲሆን፤ በሁለተኛው ዙር ከሦስት የሊግ እርከን ተወክለው የሚሳተፉ ክለቦችን በማካተት ይከናወናል። ጨዋታዎቹ ታኅሣሥ 18 እና 19/2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ይፋ በሚያደርጋቸው ሜዳዎች የሚካሄድ ይሆናል። ኅዳር 27/2017 ዓ.ም በተከናወነው የዕጣ ማውጣት ሥነሥርዓት 32 ክለቦች እርስ በርስ እንደሚጫወቱም ይፋ ሆኗል።

በዚህም 18 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ክለቦች፣ 12 የከፍተኛ ሊግ ክለቦች እና 2 የኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ ክለቦች ሦስተኛውን ዙር ለመቀላቀል ጨዋታቸውን ያደርጋሉ። በተከናወነው የዕጣ ማውጣት ሥነ-ሥርዓትም 8 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ክለቦች የቡድን አባላት ተደርገው ተጋጣሚዎቻቸውን ማወቅ ችለዋል።

በውድድሩ የሚሳተፉት ከሦስት የሊግ እርከኖች የተውጣጡ ክለቦች የሚያደርጉት ፉክክርም በጉጉት ይጠበቃል። ያለፈው ዓመት የዋንጫው አሸናፊ ኢትዮጵያ ቡና እና ሌሎች የሊጉ ክለቦች ወደ ሦስተኛው ዙር ለመቀላቀል ጠንካራ ጨዋታዎችን የሚያደርጉም ይሆናል።

በ32ቱ የሁለተኛ ዙር ተጋጣሚዎች መካከል በሚካሄዱት ጨዋታዎች 16 ሦስተኛ ዙርን የሚቀላቀሉት ክለቦች የሚለዩ ሲሆን የፕሪሚየር ሊጉ ክለቦችም እርስ በእርስ የሚያደርጉት ጨዋታም አጓጊ ነው። ኢትዮ ኤሌክትሪክ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ሐዋሳ ከተማ ከቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ድሬዳዋ ከተማ ከአርባ ምንጭ እና ኢትዮጵያ መድን ከፋሲል ከነማ የሚያደርጉት ጨዋታዎች ከፍ ያለና ጠንካራ ፉክክር እንደሚያሳዩ ከሚጠበቁት የሁለተኛ ዙር ግጥሚያዎች ቀዳሚውን ግምት አግኝተዋል። ይህም አራት የሊጉ ክለቦች በሁለተኛው ዙር እንዲሰናበቱ የሚያደርግና ጠንካራ ፉክክር የሚጠበቅበት በመሆኑ ክለቦቹ ከወዲሁ ተፈትነው ወደ ሦስተኛው ዙር እንዲቀላቀሉ መንገድ የሚከፍትላቸው ይሆናል።

በአንጻራዊነት ቀለል ያሉ ተጋጣሚዎችን የሚያስተናግዱ የፕሪምየር ሊግ ክለቦች እንዲሁ ጨዋታቸውን የሚያደርጉ ሲሆን የአምናው የውድድሩ አሸናፊ ኢትዮጵያ ቡና ከአራት ዓመት በኋላ ወደ ፕሪሚየር ሊጉ የተመለሰውን ስሑል ሽረን የሚያስተናግድ ይሆናል። በአምናው የፍጻሜ ጨዋታ በኢትዮጵያ ቡና በመረታቱ ዋንጫውን ያላሳካው ወላይታ ድቻ እንዲሁ ሦስተኛ ዙርን ለመቀላቀል በሚደረገው ፍልሚያ በተመሳሳይ ሁኔታ ከመቐለ 70 እንደርታ ይፋለማል። ሁለቱም ክለቦች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ለሦስት ዓመታት ከውድድር ርቀው እንደመመለሳቸው የአምና የፍጻሜው ተፋላሚዎች ቀለል ያለ መርሐ ግብር የደረሳቸው ይመስላል።

የጣና ሞገዶቹ ባሕርዳር ከተማዎች ከስልጤ ወራቤ፣ አዳማ ከቦዲቲ ከተማ፣ ሲዳማ ቡና ከሶሎዳ ዓድዋ፣ ሃድያ ሆሳዕና ከጋሞ ጬንቻ፣ መቻል ከአዲስ አበባ ከተማ የፕሪምየር ሊጉ ክለቦች ከሚያደርጉት ተጠባቂ ጨዋታዎች መካከል ይጠቀሳሉ። ደደቢት ከሀላባ ከተማ፣ ሽገር ከተማ ከቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ደሴ ከተማ ከአርሲ ነጌሌ፣ ሐረር ከተማ ከአምቦ ከተማ እንዲሁም ወልዋሎ አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ከሱሉልታ ክፍለ ከተማ የሚደረጉ ሌሎች የኢትዮጵያ ዋንጫ ጨዋታዎች ናቸው። በሁለተኛ ዙር የጥሎ ማለፍ ውድድር አሸናፊ የሚሆኑ ክለቦች ሦስተኛ ዙርን በመቀላቀል ለሩብ ፍጻሜ ይፋለማሉ።

በአንደኛው ዙር የኢትዮጵያ ዋንጫ ጨዋታቸውን አከናውነው ያለፉ ክለቦች ከኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ክለቦች ጋር የሚያካሄዱት የጥሎ ማለፍ ውድድር መሆኑም ተገልጿል። በዕጣ ማውጣት ሥነሥርዓቱ ላይ የቡድን አባት ሆነው ተጋጣሚዎቻቸውን ያወቁት አምና በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ባስመዘገቡት ነጥብ ነው።




የኢትዮጵያ ዋንጫ ከኢትዮጵያ ወንዶች ፕሪምየር ሊግ ቀጥሎ በኢትዮጵያ በእድሜ አንጋፋው የእግር ኳስ ውድድር ሲሆን እአአ በ1945 መካሄድ ጀምሯል። በየመሐሉ ለአስር ጊዜያት እየተቋረጠ ለ61 ጊዜ በተካሄደው ውድድር ዋንጫውን ብዙ ጊዜ ከፍ አድርጎ በማንሳት መቻል 14፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ 10፣ ኢትዮጵያ ቡና 6፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ 4፣ እና ደደቢት 2 ጊዜ ማንሳት ችለዋል።